ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 295 ሰኔ 25 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# የማዳበሪያ ግዢ እስከ መቼ?

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

**ዜና ትንታኔ**

ግብርና የተለያዩ ዘርፎች አሉት፤ በሀገራችን በሰብል እና በእንስሳት ዘርፍ የሚከናወኑ የግብርና ሥራዎች ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ። ሰፊ የመሬት ይዞታን ከመጠቀም፣ የበለጠ ትኩረት በማግኘት ብሎም ከምርታማነት አኳያ ደግሞ የሰብሉ ዘርፍ የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል። ለሰብል ምርትና ምርታማነት ወሳኝ ከሆኑ ግብዓቶች መካከል የአፈር ማዳበሪያ በቀዳሚነት ይጠቀሳል።

መንግሥት ቅድሚያ ሰጥቶ በከፍተኛ ወጪ ከሚያስገባቸው ግብዓቶች መካከልም የአፈር ማዳበሪያ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። ሀገራችን በየዓመቱ ከ700 ሚሊዮን እስከ 1 ቢሊዮን ዶላር፤ አንዳንዴም ከዚህ የበለጠ ገንዘብ ለማዳበሪያ ግዢ ታወጣለች።

ግብርና የሕዝቦቿ የሕልውና መሠረት በሆነባት ሀገር ማዳበሪያ መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ

የማዳበሪያ ግዢ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ሥዩም መኮንን

# ኢትዮጵያ በ2050 የካርቦን ልቀት መጠንን ዜሮ ለማድረስ እየሠራች ነው

መዓዛ ማሞ

ቢሾፍቱ፡- ኢትዮጵያ በ2050 የካርቦን ልቀት መጠንን ዜሮ ለማድረስ የሚያስችላትን ስትራቴጂ ነድፋ እየሠራች መሆኑን የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ገለጸ።

በዓለም አቀፍ ፋሲሊቲ እና በአረንጓዴ የአየር ንብረት ፈንድ የገንዘብ ድጋፍ በኢትዮጵያ እየተተገበሩ የሚገኙ ፕሮጀክቶች

ኢትዮጵያ በ2050 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ሀዲስ አብረሃ

ወይዘሮ ሀገረጽዮን አበበ

## በክልሉ ሳይመለስ የቆየ 136 ሚሊዮን ብር ብድር ተመላሽ ተደርጓል

- ከ17 ዓመት በላይ በሕገወጥ መንገድ የተያዙ 1300 የማምረቻ ሼዶች ተመልሰዋል

ገጽ 4

# ስተርጫ ከተማ የመጠጥ ውሃ ችግር ተስፋ የሰነቀው ፕሮጀክት

ስምስም መንግሥቱ

**ዜና ሐተታ**

በዳውሮ ዞን ተርጫ ከተማ ከፍተኛ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ችግር እንደነበርና ነዋሪው በአካባቢው ወደሚገኙ ምንጮችና ወንዞች በመጓዝ ውሃ ለመጠቀም ይገደድ እንደነበር በከተማዋ የዜሮ አንድ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ በኃይሉ ማቲዎስ ያስታውሳሉ።

በአካባቢው የነበረችው አንድ ምንጭ ከመሆኗ የተነሳ ሁሉም ወደሷ ይሄዳል፤ የንጹሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦቱ በቂ ባለመሆኑ ብልሽት ሲያጋጥም አገልግሎቱ ስለሚቋረጥ በወርና ሁለት ወር አንዴ ብቻ ነው ነዋሪው አገልግሎቱን የሚያገኘው ይላሉ።

የውሃ ችግሩ በተለይም አራስቤት ባሉ እናቶች ላይ ከፍተኛ ጫና ማሳደሩንና ችግሩም የማይረሳ እንደሆነ ነው የሚገልጹት።

በውሃ አገልግሎት ለረጅም ጊዜ ተቸግሮ የቆየው የተርጫ ከተማ ነዋሪ እፎይታ ለማግኘት መቃረቡን አቶ በኃይሉ ይናገራሉ። ከተማዋ ላይ የውሃ መሠረተ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ በመከናወኑ ልብስ ማጠብና ሰውነት መታጠብ እንደቅንጦት የሚታይበት ጊዜም እያለፈ ነው ይላሉ።

በከተማዋ ሠላም ሰፈር ተብሎ በሚጠራ መንደር ነዋሪና በሙያቸውም ጠበቃ የሆኑት አቶ በለጠ



ፎቶ - ዳኜ አበራ

ባሹ ስለተርጫ ከተማና የውሃ አገልግሎት ሁኔታ ሲያስታውሱ፤ ተርጫ ከተማ ሆና ከተመሠረተች የ20 ዓመት እድሜ እንዳላትና ቀደም ሲልም ሆነ ከተማ ሆና ከተቆረቆረች በኋላም የውሃ አገልግሎት ችግር በሰፊው ነው እንደሚስተዋል ያስረዳሉ።

ከከተማዋ 17 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከሚገኝ ዋካ ከሚባል ምንጭ በማጓጓዝና ከሚፈሱ ጅረቶች ነዋሪው ውሃ ያገኝ እንደነበነር አይዘነጉትም።

በዚህም ብዙዎች በውሃ ወለድ በሽታ ታመው ለከፋ ችግር መዳረጋቸውን የሚያስታውሱት አቶ በለጠ፤ አሁን ላይ በከተማዋ የተገነባው የውሃ መሠረተ ልማት የነበረውን ችግር እንደሚያቃልልና ከዚህ በኋላ የውሃ ጥያቄ እንደማይኖር ተስፋ አድርገናል ይላሉ።

ስተርጫ ከተማ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






መምህር ማኅደር ተስፋኪሮስ

## የክልሉን ሀብት በፍትሐዊነት በመጠቀም የኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ማስመዝገብ ይገባል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል የሚገኘውን ሀብት በፍትሐዊነት በመጠቀም የኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ማስመዝገብ የሚቻልበት መንገድ አለ ሲሉ በዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ የአካውንቲንግና ፋይናንስ መምህር የሆኑት መምህር ማኅደር ተስፋኪሮስ ተናገሩ።

መምህር ማኅደር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ ትግራይ ክልል ውስጥ በተለይ በቱሪዝምና በማዕድን የሚገኝ ገቢ በሥርዓትና በፍትሐዊ መንገድ ማስተዳደር ከተቻለ ለወጣቱ የሥራ ዕድል ከመፍጠር ባለፈ ኢኮኖሚውን ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወጣት በተለያዩ ምክንያቶች ሥራ አጥ ሆኗል ያሉ ሲሆን፤ የዚህ ምክንያት ደግሞ ከጦርነቱ ወዲህ የተፈጠረው ድባቴና የኢኮኖሚ ችግር ነው ብለዋል።

በመሆኑም ይህን ችግር ለመፍታትና ክልሉ ውስጥ የኢኮኖሚ መሻሻል ለማምጣት፤ በክልሉ ያለውን ሀብት በፍትሐዊነት መጠቀም እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

በተጨማሪ የወጣቱ የሥራ ዝንባሌ በመረዳት ሥልጠና መስጠት እንዲሁም በውስጡ ያለው ጭንቀት እንዲያስወግድ መንግሥት እጁ በማስገባት በትኩረት ሊያየው ይገባል ብለዋል።

መምህሩ እንደተናገሩት፤ የክልሉን የቱሪዝም ፀጋዎች በተለይም ገረዓልታ፣ አክሱም፣ ይሓ፣ አብርሃ ወአፅበሃ እንዲሁም የተለያዩ ሰው ሠራሽ መስሕቦችን ወደ ኢኮኖሚያዊ ገቢ በመቀየር፣ ወጣቱ በማደራጀት እንዲሁም የክልሉ ፀጥታ እንዲሻሻል በማድረግ ገቢውን ማሳደግ ይቻላል።

በተጨማሪም በርካታ ማዕድኖች በክልሉ ይገኛሉ ያሉት መምህሩ፤ በፍትሐዊነት ማዕድን የማውጣት ሥራ ላይ ወጣቱ እንዲሠማራ በማድረግ ገቢው እንዲሻሻል ጥረት ማድረግ ይገባል ሲሉ አስረድተዋል።

ወጣቱን ተጠቃሚ ለማድረግ አሁን የሚስተዋሉ ኢ-ፍትሐዊ አካሄዶችን በማስተካከል ረገድ መንግሥት በዘላቂነት ምቹ መዋቅር መዘርጋት አለበት ብለዋል።

አሁን ላይ የተወሰኑ ወጣቶች በእርሻ፣ በአነስተኛ ትናንሽ ኢንዱስትሪ ውስጥ በመደራጀት ተስፋ የሚሰጥ ሥራ የሚሠሩ አሉ፤ ወጣቶቹ የብድር አቅርቦት፣ የገበያ ትስስርና ሌሎች ችግሮች ያጋጥማቸዋል ሲሉ አንስተዋል።

በመሆኑም ችግሮቻቸው እንዲፈቱና የገበያ ትስስር እንዲኖራቸው መሥራት እንዳለበት አመላክተዋል።

የተፈጠረው የኢኮኖሚ ችግር ለመፍታትና መሻሻል እንዲመጣ በተለይ የተማረ የሰው ኃይል ድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ ጠቅሰው፤ አሁን ያለው ችግር እንዳይባባስ ወጣቱ ስደት ከመሄድና ከሥራ አጥነት እንዲላቀቅ ከመንግሥት ጋር በመሆን የመፍትሔ አካል ሊሆን ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

# የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በትብብር መሥራት ያስፈልጋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ መንግሥት፣ የግሉ ዘርፍና ወጣቶች በትብብር መሥራት እንደሚገባቸው የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) ገለጹ።

የኢትዮጵያ ሥራ ፈጣሪ ወጣቶች ማኅበርና የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በትብብር ያዘጋጁት "ዘለላ 10 አንድ ጉዳይ" የተሰኘ መድረክ ትናንት ተካሂዷል።

ሚኒስትሯ ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) በመድረኩ ላይ እንዳመለከቱት፤ የወጣቶችን አቅም ማጎልበትና ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ለአንድ ሀገር እድገት ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

በመሆኑም ለወጣቶች ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠርና ሁለንተናዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ መንግሥት፣ የግሉ ዘርፍና ወጣቶችም ጭምር በትብብር መሥራት ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ዛሬ ላይ ለወጣቶች ያልሠጠናቸውን ዕድል ነገ ልንጠይቃቸው አንችልም ያሉት ሚኒስትሯ፤ የወጣቶችን የማሰብና ችግሮችን ወደ ዕድል የመለወጥ አቅም ለማጎልብት መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል። ለዚህ ደግሞ ከመንግሥት ብቻ መጠበቅ ሳይሆን የግሉ ዘርፍና ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችም ሚናቸውን መወጣት እንዳለባቸው አንስተዋል።

ወጣቶችም በተበታተነ መልኩ ከመንቀሳቀስ ይልቅ በመደራጀትና በትብብር በመሥራት የሚጠበቅባቸውን



ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር)

ኃላፊነት መወጣት፣ የጎደላቸውን መጠየቅ እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

መንግሥት የወጣቶችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን አስታውሰው፤ ሀገራዊ የወጣቶችን ፖሊሲ ዘመኑን በሚዋጅ መልኩ ለማሻሻል እየተሠራ ነው ብለዋል።

አሁን ላይ ዝግጅቱ ተጠናቆ ወደሚመለከታቸው አካላት የተላከ ስለሆነ በሚቀጥለው ዓመት ፀድቆ ወደ ሥራ ይገባል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል።

ወጣቶች ትልቅ የለውጥ አቅም መሆናቸውንና ለአንድ ሀገር እድገት ያላቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ወጣቶች በበጎ ፈቃድ ሥራዎችና በዜግነት አገልግሎት በመሳተፍ ሀገራቸውን እንዲያገለግሉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠሩን አመላክተዋል።

ለወጣቶች ምቹ ሁኔታ መፍጠር ለአንድ ተቋም ብቻ የሚተው ባለመሆኑ ሁሉም ባለድርሻዎች በቅንጅት መሥራት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ሥራ ፈጣሪ ወጣቶች ማኅበር ፕሬዚዳንት ወጣት ሳሚያ አብዱልቃድር በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ማኅበሩ የመንግሥትና ሌሎችም አጋር አካላት በሮች ለወጣቶች ክፍት እንዲሆኑ ለማስቻልና መሰናክሎቻቸውን ለመቅረፍ ይሠራል።

በዚህም ከብዙ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ትብብር መፍጠር ችሏል፤ በአንድ ጥላ ሥር መሰባሰባችንም ድምፃችን ጎልቶ እንዲሰማ ዕድል ፈጥሮልናል ብለዋል።

የዘለላ አንድ ጉዳይ ውይይቶችም በወጣቶች ሥራና ዕድሎች ላይ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በማንሳት እስከ ፖሊሲ ማስቀየር የሚደርስ ተፅዕኖ ለመፍጠር የሚደረግ ምክክር መሆኑን አመላክተዋል።

ከውይይቱ ጎን ለጎን የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ሥራ ፈጣሪ ወጣቶች ማኅበር በትብብር መሥራት የሚያስችላቸውን የመግቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።

# ኢትዮጵያ ሠላምና መረጋጋት እንዲሰፍን አይተኬ ሚና ተጫውታለች

- ብርጋዴር ጄኔራል ፖል ካሁሪያ ጀማ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ተጠንቀቅ ኃይል አባልነቷ በቀጣናው ሠላምና መረጋጋት እንዲሰፍን አይተኬ ሚና መጫወቷን የምሥራቅ አፍሪካ የተጠንቀቅ ኃይል ዳይሬክተር ብርጋዴር ጄኔራል ፖል ካሁሪያ ጀማ ገለጹ።

በኬንያ ናይሮቢ ከሚገኘው የምሥራቅ አፍሪካ ተጠንቀቅ ኃይል ቢሮ የተውጣጣ ልዑክ ኢትዮጵያን ለምሥራቅ አፍሪካ ተጠንቀቅ ኃይል የምታዋጣውን ሞተራይዝድ ሻለቃ የግዳጅ ዝግጁነት የሚያረጋግጥ ቡድን ወደ ኢትዮጵያ ገብቷል።

ቡድኑ ለሁለት ቀናት የሚቆይ የቅድመ ዝግጁነት ማረጋገጥና ግምገማ መድረክ በቢሾፍቱ ከተማ ማካሄድ ጀምሯል።

በመድረኩ የምሥራቅ አፍሪካ ተጠንቀቅ ኃይል ዳይሬክተር ብርጋዴር ጄኔራል ፖል ካሁሪያ ጀማ እና የኢፌዴሪ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ወታደራዊ አማካሪና የተኩስ አመራር ኃላፊ ሌተናል ጄኔራል ዓለምእሸት ደግፌን ጨምሮ የተጠንቀቅ ኃይሉ አመራሮችና ወታደራዊ መኮንኖች፣ የሲቪል ሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም የአፍሪካ ኅብረት ተወካዮች ተገኝተዋል።

ብርጋዴር ጄኔራል ፖል ካሁሪያ ጀማ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ለምሥራቅ አፍሪካ ተጠንቀቅ ኃይል ሙያዊነትን የተላበሰና ብቁ ሠራዊት በማዋጣት አይተኬ ሚና አበርክታለች።

ኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ አስተዋፅዖ በመወጣት የምትታወቅ ሀገር ስለመሆኗም ጠቅሰዋል።

ለምሥራቅ አፍሪካ ሠላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ትልቅ ልምድና ተሞክሮ ያላት ሀገር መሆኗን ገልጸው፣ እስካሁንም ኢትዮጵያ በተሠማራችበት ተልዕኮ ሁሉ ለነበራት ወሳኝ አበርክቶ ምስጋና ችረዋል።

በቀጣይም በቀጣናው ሀገራት ትብብርን በማጠናከር ዘላቂ ሠላምና መረጋጋት እንዲሰፍን



ብርጋዴር ጄኔራል ፖል ካሁሪያ ጀማ



ሌተናል ጄኔራል ዓለምእሸት ደግፌ

በቁርጠኝነት መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል።

የኢፌዴሪ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ወታደራዊ አማካሪና የተኩስ አመራር ኃላፊ ሌተናል ጄኔራል ዓለምእሸት ደግፌ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ምንጊዜም ለአፍሪካና ለቀጣናው ሠላምና ፀጥታ በትብብር በመሥራት ቁልፍ ሚና የምትጫወት ሀገር መሆኗን ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያ ለተጠንቀቅ ኃይሉ እንደ መሥራች ሀገር በእስካሁን ታሪኳ በሀሳብ አመንጪነት ብቻ ሳይሆን በተግባር ግንባር ቀደም ተዋናይ ሆና መቀጠሏን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በፋይናንስ ረገድም ትልቅ በጀት መድባ ለቀጣናው ሠላም መስፈን እንደሠራችም ጠቅሰዋል።

የተጠንቀቅ ኃይሉ አቅም እንዲጠናከር ሁሉን አቀፍ ዝግጁነት እንዲኖረውና ተልዕኮውን በብቃት እንዲወጣ ኢትዮጵያ ያላትን ቁርጠኝነትና ዝግጁነት አንስተዋል።

የቀጣናው ሀገራት በሁሉም መስክ ዘርፎች ትብብር እንዲጠናከር ተጠንቀቅ ኃይሉ ሠላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ትልቅ ሚና እንዳለው ጠቅሰው፤ በዚህም የኢትዮጵያ ሞተራይዝድ ሻለቃው ሁልጊዜም ዝግጁ እንደሆነ ገልፀዋል።

ኢትዮጵያ በቀጣናው የተሻለ ነገ እንዲመጣና የአካባቢው ሕዝብ የሚመኘውን ሠላምና ብልፅግና በዘላቂነት ለማረጋገጥ አይተኬ ሚናዋን አጠናክራ እንደምትቀጥል አረጋግጠዋል።

የተጠንቀቅ ኃይሉ ልዑክ በኢትዮጵያ ቆይታው የኢትዮጵያን የምሥራቅ አፍሪካ ተጠንቀቅ ኃይል ሞተራይዝድ ሻለቃ ጠቅላይ ጦር ሰፈር ተገኝቶ የሻለቃን ዝግጅትና ቁመና እንደሚመለከትም ይጠበቃል።

# ሀገራዊ የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን ተገልጋይ ርካታ 68 በመቶ ደርሷል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዳማ፡- በጤና መድኅን አገልግሎት ሥር የሚሰጠው የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን የተገልጋይ እርካታ በሀገር አቀፍ ደረጃ 68 በመቶ መድረሱ ተገለጸ። በአዲስ አበባ ያለው የአገልግሎት ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑንም ጥናት ጠቁሟል።

በማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ተገልጋዮች እርካታ፣ ግንዛቤ እና አመለካከት ዙሪያ የተጠና ጥናት ትናንት ይፋ ተደርጓል።

በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጤና፣ ማኅበራዊና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ ወርቀሰሙ ማሞ፤ በጤና መድኅን አገልግሎት ሥር የሚሰጠው የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን ተገልጋይ እርካታ፣ ግንዛቤ እና አመለካከት ዙሪያ የተጠናው ጥናት የክትትልና ቁጥጥር ሥራችንን እንድናጠናክር ይረዳናል ሲሉ ተናግረዋል።



ወይዘሮ ወርቀሰሙ ማሞ

ወይዘሮ ወርቀሰሙ በመርሐግብሩ መክፈቻ ላይ እንዳሉት፤ በማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን ተገልጋይ እርካታ ዙሪያ የተጠናው ጥናት የተጠቃሚውን ሕዝብ እርካታ በነሲብ ሳይሆን በሳይንሳዊ ጥናት ላይ በተመሠረተ መልኩ እንዲታይ ያደርገዋል። ይህም የክትትልና ቁጥጥር ሥራውን ለማጠናከር ይረዳል ብለዋል።

በዘርፉ ተገልጋዮች በወረፋ እንዳይጉላሉ ለብቻቸው አንድ መስኮት ተዘጋጅቶላቸው እንዲጠቀሙ መደረጉ ለአብነት የሚጠቀስ እርካታን የሚያሳድግ ተግባር መሆኑን ጠቅሰው፤ ሆኖም ከዚህ የተሻለ ርካታን ለመፍጠር በመድኃኒት ግዢ ላይ የሚታዩ ክፍተቶች ሊስተካከሉ ይገባል ብለዋል።

የጤና መድኅን አገልግሎት ዜጎች በችግር ምክንያት ሳይታከሙ እንዳይቀሩ በፓይለት ደረጃ በጥቂት ወረዳዎች መጀመሩን አንስተው፤ በፓይለት ደረጃ የተወጠነው ውጤታማ መሆኑን ተከትሎ ወደ ትግበራ መግባት መቻሉን አብራርተዋል።

አሁን ባለበት ደረጃ የአገልግሎቱ ሽፋን ጥሩ የሚባል መሆኑን የጠቀሱት ወይዘሮ ወርቀሰሙ፤ በተገልጋዩ ርካታ ላይ ይበልጥ ሊሠራ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ በተለይ የመድኃኒት አቅርቦት ችግር ማነቆ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዚህ ምክንያት የመድኅን አገልግሎቱ ወደኋላ እንዳይመለስ ስጋት አለኝ ሲሉ ተናግረዋል።

ጥናቱን ያቀረቡት በአገልግሎቱ የፈንድ ስጋትና የኢንቨስትመንት መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ አዳሙ ወንድምተካ በበኩላቸው፤ በሥርዓቱ 12 ሚሊዮን አባወራና እማወራዎች ተጠቃሚ መሆናቸውን ጠቅሰዋል። 56 ሚሊየን ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉንም ተናግረዋል።

ጥናቱ በስምንት ክልሎች የተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ሀገራዊ የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች እርካታ 68 በመቶ መድረሱን በጥናቱ አመላክተዋል።

ዝቅተኛው የተገልጋዮች እርካታ በደቡብ ክልል የተመዘገበ ሲሆን፤ ከፍተኛው የተገልጋዮች እርካታ ደግሞ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ስለመሆኑም በጥናቱ ተመላክቷል።

ማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን አገልግሎት ግንዛቤ በሀገር አቀፍ ደረጃ 63 በመቶ እንደሆነም በጥናቱ ተጠቅሷል።

በጥናቱ በተመላከተው መሠረት ስለአገልግሎቱ ዝቅተኛ ግንዛቤ የተመዘገበባቸው አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ሲሆኑ ከፍተኛው ግንዛቤ የተመዘገበው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና ኦሮሚያ ክልሎች ነው።

በማኅበረሰብ አቀፍ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ዘንድ እርካታ ዝቅ እንዲል ካደረጉት መካከል የመድኃኒት አቅርቦትና የላቦራቶሪ አገልግሎቶች ተጠቃሽ መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል።

የኢትዮጵያ የጤና መድኅን አገልግሎት ዜጎች እንዳቅማቸው አዋጥተው እንደሕመማቸው እንዲታከሙ እና የዓለም የጤና ድርጅት ያስቀመጠውን የጤና ሽፋን ለማዳረስ የተቀረፀ የዚሁ አካል የሆነው የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን ሥርዓት የሙከራ ትግበራውን የጀመረው በ2013 በሦስት ወረዳዎች ነበር። በተያዘው 2016 በጀት ዓመት 1052 ወረዳዎችን በመሸፈን ከ54 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረጉን መረጃዎች ያሳያሉ።



ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ



አይናለም ንጉሤ

# መጪውን ትውልድ ታሳቢ ያደረገ ጠንካራ የታክስ እውቀት እንዲኖር እየተሠራ ነው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- መጪውን ትውልድ ታሳቢ ያደረገ የታክስ እውቀት ላይ የተመሠረተ አመራር ለመስጠት በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተሠራ መሆኑን የገቢዎች ሚኒስቴር አስታወቀ። ሀገራዊ የተማሪዎች የታክስና ቀረጥ የአሸናፊዎች አሸናፊ ውድድር ተካሂዷል።

ትኩረቱን ታክስና ቀረጥ ላይ ያደረገ የተማሪዎች የአሸናፊዎች አሸናፊ ውድድር ትላንት በአዲስ አበባ የተካሄደ ሲሆን፤ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተወጣጡ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በውድድሩ ተሳትፈዋል። በውድድሩ አሸናፊ ለሆኑና ከአንደኛ እስከ 10ኛ ደረጃን ለያዙ ተማሪዎች የላፕቶፕ እና ስልክ እንዲሁም ለአብቂ መምህራንና ርዕሳነ መምህራን የብር ሽልማት በተጨማሪም ተማሪዎቹ ለወከሏቸው ትምህርት ቤቶች የኮምፒዩተር ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

በውድድር መድረኩ ንግግር ያደረጉት የገቢዎች ሚኒስትር ወይዘሮ አይናለም ንጉሤ የጥያቄና መልስ ውድድሩ ባለፈው ዓመት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የከፈቱትና እስካሁን ድረስ እየተከናወነ የሚገኘው የ"ግብር ለሀገር ክብር" ንቅናቄ አካል እንደሆነ ጠቅሰዋል። ይህም መጪውን ትውልድ ታሳቢ ያደረገ የታክስ እውቀት ላይ የተመሠረተ አመራር ለመስጠት እየተሠራ እንዳለ ማሳያ ነው ብለዋል።

ተወዳዳሪ ተማሪዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ካሉ 240 በላይ ትምህርት ቤቶች ተወዳድረውና ከእያንዳንዱ ክላስተር አሸንፈው ለመጨረሻው ሀገራዊ ውድድር የቀረቡ መሆናቸውን ገልጸዋል። ውድድሩም ጠንካራ የታክስ እውቀት ያለው፣ በሥነ ምግባር የታነጸና ሀገር ለመቀየር የሚተጋ ትውልድ እንዲኖር ትልቅ ሚና ያለው ነው ብለዋል።

ውድድሩ ሲካሄድ በእያንዳንዱ የተቋሙ ሥራ ውስጥ የታክስ ሞራል ያለው፣ ለታክስ ሕጉ ተገዢ የሆነ፤ ሌብነትን የሚጸየፍ ትውልድ መገንባት እንደሚያስፈልግ ታሳቢ በማድረግ ነው በማለት፤ ለሁሉም የማኅበረሰብ ክፍልና ለመጪው ትውልድ የሚጋባ በእውቀት ላይ የተመሠረተ አመራር ለመስጠት የሚያስችል ሥራ እየተሠራ እንዳለ አመላክተዋል።

የጉምሩክ ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ በበኩላቸው፤ "ግብር ለሃገር ክብር" በሚል መሪ ቃል ከፌዴራል እስከ ታችኛው የመንግሥት መዋቅር ድረስ የታክስ እና የጉምሩክ ሕግ ተገዥነት የንቅናቄ መድረክ ሲካሄድ መቆየቱን ገልጸዋል። በዚህም በሃይማኖት ተቋማት፣ በትምህርት ቤቶች እና በሌሎች ሕዝባዊ ተቋማት የታክስ ስርጸትን ለማሳደግ የሚያስችሉ በርካታ ውይይቶች እና የንቅናቄ መድረኮች መከናወናቸውን ተናግረዋል።

የተማሪዎች ጥያቄና መልስ ውድድሩ የዚህ ንቅናቄ አንዱ አካል መሆኑን የጠቀሱት ኮሚሽነሩ፤ ውድድሩ ስለ ታክስና የጉምሩክ ሕጎች በቂ ግንዛቤ ያለው ትውልድ ለማፍራት ፋይዳው የጎላ እንደሆነ ገልጸዋል።

በጉምሩክና በታክስ ጥያቄና መልስ ውድድር ተማሪ ሕሊና ተክለማርያም ከመቀሌ አንደኛ ስትወጣ፤ ተማሪ ሲቲና አሕመድ ከኩታበር ሁለተኛ እንዲሁም ተማሪ ሲና አበራ ከጅግጅጋ ሦስተኛ በመሆን ሽልማታቸውን ተቀብለዋል። ውድድሩ ቀጣይነት ያለውና በየዓመቱ የሚካሄድ መሆኑም ተገልጿል።

በአሸናፊዎች አሸናፊ የጥያቄና መልስ ውድድሩ የገቢዎች ሚኒስትር አይናለም ንጉሤ፣ የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ ምክትል ኮሚሽነሮች፣ ዳይሬክተሮች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች እና የተማሪ ወላጆች ተገኝተዋል።

# በዩኒቨርሲቲዎች በሚሠሩ ጥናቶች

## ላይ አሳስፈላጊ ድግግሞሽና ሀብት ብክነትን ማስቀረት ይገባል

**መስከረም ሰይፉ**



አዲስ አበባ፡- በዩኒቨርሲቲዎች በሚሠሩ ጥናቶች ላይ የሚስተዋሉ አላስፈላጊ ድግግሞሽና ሀብት ብክነትን ማስቀረት እንደሚገባ የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቶች ገለጹ።

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት አሥራት አፀደወይን (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ ዘርፎች የተለያዩ የጥናትና ምርምሮችን ይሠራል።

ብዙ ጊዜ በዩኒቨርሲቲዎች የሚሠሩ ጥናትና ምርምሮች ተግባራዊነት ላይ ጥያቄ እንደሚነሳ የገለጹት አሥራት (ዶ/ር) ፤ ዩኒቨርሲቲው ይህንን ለመመለስ ሊታተሙና ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ ለሚታሰቡ ጥናትና ምርምሮች ቅድሚያ እንደሚሰጥ ገልጸዋል።

በዚህም በአሁኑ ወቅት እየተሠሩ ያሉ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በዓለም አቀፍ ጆርናሎች እንዲታተሙ እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

በዩኒቨርሲቲዎቹ የሚሠሩ ጥናቶች ላይ ብዙ ክፍተት የሚታይ ቢሆንም ዋነኛው ችግር ግን እንደ ሀገር የሚሠሩ ጥናቶችን መሰብሰብና መረጃ መለዋወጥ አለመቻል መሆኑን ገልጸዋል።

ይህም በአንድ ጉዳይ ላይ አላስፈላጊ ድግግሞሾችን በመፍጠር ለሀብት ብክነት እያጋለጠ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች የሚሠሯቸው ጥናቶች በአንድ ላይ የሚያስቀምጡበት መንገድ መፍጠር ላይ ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች አተኩረው ሊሠሩ እንደሚገባ ገልጸዋል።

ፕሬዚዳንቱ ጎንደር ዩኒቨርስቲ በአሁኑ ወቅት አተኩሮ ከሚሠራባቸው ዘርፎች አንዱ የአየር ንብረት ለውጥ ነው ያሉ ሲሆን በተለያዩ የትምህርት መርሐግብሮች ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ቁርኝት ያላቸው ትምህርቶች እንዲሰጥ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ከዚህ በተጨማሪም የአየር ንብረት ለውጥን እንደ መዋቅር አዘጋጅቶ ማዕከል መክፈቱንና በዚህ ማዕከልም ሙሉ በሙሉ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያያዥ የሆኑ የጥናትና ምርምሮች እንዲሁም ችግሩን ሊያቃልሉ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች ላይ እንደሚሠራ አብራርተዋል።

ለአብነትም በዩኒቨርስቲው በጣና ሐይቅ ይስተዋል የነበረውን እንቦጭ አረምን ወደ ማዳበሪያነትና ለመብራትነት እንዲያገለግል የሚያስችል ቴክኖሎጂን መሥራቱን ጠቅሰዋል።

ሌላኛው ኢፕድ ያነጋገራቸው የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ኡባህ አደም (ዶ/ር) በበኩላቸው ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ከመማር ማስተማር ጎን ለጎን የማኅበረሰቡን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ የተለያዩ ጥናትና ምርምሮችን እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

እንደ ሀገር ዩኒቨርሲቲዎች የሚሠሯቸው ጥናቶች የሚያስተዋውቁበትና የሚወያዩበት መንገድ አነስተኛ ነው ያሉ ሲሆን ይህም ተደጋጋሚ ጥናት እንዲሠራ ምክንያት እየሆነ ይገኛል ብለዋል።

ኡባህ (ዶ/ር)፤ ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲም በአሁኑ ወቅት ወደ መሬት ቢወርዱ ለውጥ ያመጣሉ በሚላቸው እንደ ጎርፍ የመሰሉ የድሬዳዋ ችግሮች ላይ ያተኮሩ ጥናቶች እንዲሠሩ በበጀት ጭምር ቅድሚያ እየሰጠ እየሠራ ለከተማ አስተዳደሩ እየሰጠ መሆኑን ገልጸዋል።

ነገር ግን በዩኒቨርሲቲው የሚሠሩ የተለያዩ ጥናቶች ወደ መሬት ወርደው መፍትሔ እንዲያመጡ ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር መረጃ የመለዋወጥና የመናበብ ችግር መኖሩን አንስተዋል።

# በክልሉ ሳይመለስ የቆየ 136 ሚሊዮን ብር ብድር ተመላሽ ተደርጓል

## - ከ17 ዓመት በላይ በሕገወጥ መንገድ የተያዙ 1300 የማምረቻ ሼዶች ተመልሰዋል

**ሶሎሞን በየነ**

ሃዋሳ፡- ቀደም ሲል ለወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ ተሰጥቶ ሳይመለስ ተበልቶ ከቀረው ውዝፍ ብድር ውስጥ 136 ሚሊዮን ብር በተያዘው በጀት ዓመት በ10 ወራት ውስጥ ማስመለሱን የሲዳማ ክልል የሥራ ክህሎት እና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ገለጸ። በክልሉም ከ17 ዓመት በላይ በሕገወጥ መንገድ የተያዙ 1300 የማምረቻ ሼዶችና የምርት መሸጫ ኮንቲነሮችን በ10 ወራት ውስጥ በማስመለስ ለሥራ ፈላጊ ወጣቶች መሰጠቱ ተጠቁሟል።

የቢሮው ኃላፊ ወይዘሮ ሀገረጽዮን አበበ በክልሉ የሥራ ምልከታ ላደረጉ የጋዜጠኞች ቡድን እንደተናገሩት፤ እንደ ክልል ለሥራ ዕድል ፈጠራ ተሰጥቶ ሳይመለስ የቀረ 400 ሚሊዮን ብር ውዝፍ ብድር አለ። ከዚህ ውስጥ በ2016 በጀት ዓመት 160 ሚሊዮኑን ለማስመለስ ታቅዶ፤ በ10 ወራት ውስጥ ለወጣቶች የሥራ እድል ፈጠራ ተሰጥቶ ሳይመለስ ተበልቶ ከቀረው ውዝፍ ብድር ውስጥ 136 ሚሊዮን ብር ማስመለስ ተችሏል።

"በሥራ ዕድል ፈሠራ ሥራ ውስጥ በጣም ትልቁ ፈተና ብድር ማስመለስ ነው" የሚሉት የቢሮ ኃላፊዋ፤ ቀደም ባለው ጊዜ ለሥራ ዕድል ፈጠራ ብድር ተሠራጭቶ የወሰደው አካል የማይታወቅ፣ የጠፋ አለ። በአንጻሩ ደግሞ መንግሥት ሠራተኛ፣ አመራር፣ ባለሀብት ... ወዘተ ብድር መውሰዳቸው እየታወቀ የማይጠየቁበትና የማይነኩበት ሁኔታ አለ። ሆኖም እንደ ክልል ውዝፍ ብድር ላይ ያለውን ትልቅ አቅም አሟጦ መጠቀም ቢቻል፤ ለብዙ ሥራ ፈላጊ ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚቻልበት ዕድል እንዳለ ያስረዳሉ።

ወይዘሮ ሀገረጽዮን ይህንን እድል አሟጦ ለመጠቀም ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ በፍትሕ አካላት የሚመራ ብድር አስመላሽ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ውዝፍ ብድር የማስመለስ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመው፤ ግብረ ኃይሉ ብድር ወስደው ያልመለሱ አካላትን "እገሌ እገሌ" ሳይል ሁሉንም ሕግ ፊት በማቅረብ ንብረት እስከ መውረስና ማሰር ድረስ ርምጃ እየወሰደ ይገኛል። የጠፉትንም እያፈላለገ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በዚህም ውዝፍ ብድር የማስመለስ አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል ያሉት የቢሮ ኃላፊዋ ወይዘሮ ሀገረጽዮን፤ ለወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ ተሰጥቶ ሳይመለስ ተበልቶ ከቀረው ውዝፍ ብድር ውስጥ 90 ሚሊዮን ብር በ2015 ዓ.ም ማስመለስ ተችሏል። በተመሳሳይ በ2016 በጀት ዓመት 160 ሚሊዮን ብር ለማስመለስ ታቅዶ፤ በ10 ወራት ውስጥ 136 ሚሊዮን ብር ውዝፍ ብድር ማስመለስ ተችሏል። በቀጣይም ውዝፍ ብድር የማስመለስ ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

የማምረቻና የምርት መሸጫ ሼዶች የሥራ ፈላጊ ወጣቶች አንገብጋቢ ጥያቄ እንደሆነ ወይዘሮ ሀገረጽዮን ገልጸው፤ የመሥሪያ ሼዶችን ከመገንባት ባለፈ ከዚህ በፊት በሕገወጥ መንገድ የተያዙትን አስመልሶ ለሥራ ፈላጊዎች ከመስጠት አንፃር ሰፊ ሥራ ተሠርቷል። ከዚህ አኳያ በዚህ ዓመት በ10 ወራት ውስጥ በሕገወጥ መንገድ እስከ 17 ዓመት ድረስ ተይዘው የነበሩ 1300 የማምረቻ ሼዶችን በማስመለስ እና አዲስ 300 ሼዶችን በመገንባት በድምሩ 1600 የመሥሪያ ሼዶች ለወጣቶች ተሰጥቷል ብለዋል።

እንዲሁም የማይገባቸው ሰዎች ይዘውት የነበረ 50 ሄክታር መሬት በማስመለስ፤ በ10 ወራት ውስጥ ከ800 በላይ ሄክታር መሬት ለወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ ተሰጥቷል። በዚህም ከየትኛውም ዓመት የበለጠ በ2016 ዓ.ም ከፍተኛ የመሥሪያ ሼዶችና መሬት ለወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ መሰጠቱን ተናግረዋል።

የቢሮ ኃላፊዋ በባንኮችና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት የቀረበው ሳይጨመር በመንግሥት ብቻ 175 ሚሊዮን ብር ብድር በ10 ወራት ውስጥ ለወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ መሰጠቱን ጠቁመው፤ መንግሥት በማይክሮ ፋይናንስ ከሚያቀርበው ብድር ባሻገር ከባንኮች ጋር የማስተሳሰር ሥራ ጎን ለጎን እየተሠራ ነው። የወቅቱን የገበያ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የብድር ጣሪያው መሻሻሉን፤ ከ49 ሺ. በላይ ወጣቶች አጫጭር ገበያ ተኮር ተሰጥቷቸው ወደ ሥራ መግባታቸውን አመላክተዋል።

እየተገባደደ ባለው በጀት ዓመት 7500 በላይ ኢንተርፕራይዞችን ለማሸጋገር ታቅዶ፤ 6000 ኢንተርፕራይዞች ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፤ ከአነስተኛ ደግሞ ወደ መካከለኛ ተሸጋግረዋል ብለዋል።

ምንም አይነት የውሸት ሪፖርት ሳይታከልበት በተጨባጭ መሬት ላይ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸው ከዳቦ በላይ ሕይወታቸውን እየቀየሩ ላሉ 53 ሺህ ዜጎች በ10 ወራት ውስጥ ቋሚ የሥራ ዕድል እንደተፈጠረላቸው ተመላክቷል።

# የማዳበሪያ ግዢ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ባይሆንም፣ ማዳበሪያን በራሳችን አቅም የማምረት አቅም የለንም ወይ? በየጊዜው ለማዳበሪያ ግዢ የምናወጣውን ወጪ ለምን መቀነስ ተሳነን? ኢትዮጵያ ማዳበሪያን በራሷ አቅም ማምረት ብትችል ምን ፋይዳ ያስገኝላታል? ከመንግሥት በኩልስ እንዴት ያለ ጥረት ይጠበቃል?

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የአፈር ተመራማሪው ብሩ ይታፈሩ (ዶ/ር)፣ በሀገራችን በዋናነት ተፈላጊ የሆኑት ዩሪያና ዳፕ የተሰኙት የማዳበሪያ አይነቶች መሆናቸውን ይናገራሉ፤ ማዳበሪያዎቹ ናይትሮጂንና ፎስፌት ከተሰኙ ንጥረ ነገሮች የሚገኙ መሆናቸውንም ያነሳሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፣ ማዳበሪያን ማምረት በቂ ጥሬ እቃና ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይልን ይጠይቃል። ቀደም ባሉ ጊዜያት ሀገራችን በቂ የኃይል አቅርቦት የነበራት ባትሆንም፣ በአሁኑ ሰዓት ግን ከፍተኛ መጠን ያለው የኤሌክትሪክ ኃይልን እያመነጨች ትገኛለች። ከኤሌክትሪክ ኃይል በተጨማሪ፣ ዩሪያ የሚባለውን ማዳበሪያ በሀገር ውስጥ ለማምረት በሱማሌ ክልል ኦጋዴን አካባቢ የተገኘው ጋዝ አንዱ ግብዓት ሲሆን፣ ምዕራብ ኢትዮጵያ ላይ የተገኘው የድንጋይ ከሰል ሌላኛው ግብዓት ነው።

ከዚህ አንጻር፣ መንግሥት ኢንዱስትሪው ላይ ትኩረት አድርጎ ቢሠራ፣ የሀገራችንን ዕጣ ፈንታ የሚወስነውንና ጥቅም ላይ ከሚውሉ ማዳበሪያዎች መካከል ከ65 እስከ 70 ከመቶ የሚሆን ድርሻ ያለውን ዩሪያ ማዳበሪያ በሀገር ውስጥ ማምረት እንችላለን።

በኢትዮጵያ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት የተፈጥሮ ሀብትና የአየር ንብረት ፕሮግራም ዶ/ር አወቀ ሙሉዓለም (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ የግብርናውን ምርትና ምርታማነት ለመጨመር ማዳበሪያ ቀዳሚው ግብዓት መሆኑን አንስተው፣ መሬታችንን የበለጠ በተጠቀምን ቁጥር፣ ለሰብል እድገት ምግብ የሆኑ አፈር ውስጥ ያሉ ንጥረ ነገሮች እየተመናመኑ እንደሚሄዱ ያስረዳሉ። ይህን ለመተካት ማዳበሪያ መጨመር የግድ አስፈላጊ መሆኑ ላይም ያሰምሩበታል።

የኢትዮጵያ የምርት ጭማሪ በአብዛኛው የተንጠለጠለው በማዳበሪያ ላይ ነው ያሉት አወቀ (ዶ/ር)፣ በሰብል ምርት ከ60 እስከ 80 የምርት ጭማሪ ማግኘት የምንችለው ማዳበሪያ ስንጠቀም ነው ይላሉ። ይህ መሠረታዊ የግብርና ግብዓት ፍላጐት በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ መሆኑ ላይም ያሰምሩበታል።

የማዳበሪያን ጥቅም ከሁሉም በበለጠ የተረዳው አርሶ አደሩ ነው ያሉት አወቀ (ዶ/ር)፣ ማዳበሪያን ተጠቅሜ ካልዘራሁ ምርት አላገኝም የሚል ግንዛቤ መዳበሩን አንስተዋል።

አሁን ላይ የማዳበሪያን ጥቅም ከማስተዋወቅ አልፈን የሚፈለገውን ያህል አቅርቦት ማቅረብ የተቸገርንበት ሁኔታ ላይ ነን ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ይህን ችግር ለመቅረፍ ማዳበሪያን በሀገር ውስጥ ማምረት መፍትሔ ነው የሚል አስተያየት ይሰጣሉ። ልክ እንደ ብሩ (ዶ/ር)ሁሉ ዩሪያ ማዳበሪያን ለማምረት የሚያስችል የተፈጥሮ ጋዝ እንዳለን አንስተው በሀገራችን ሶማሌ ክልል ኦጋዴን ላይ ያለውን የተፈጥሮ ጋዝም ጠቅሰዋል።

መንግሥት ማዳበሪያ ከምንም ነገር በላይ ወሳኝ መሆኑን አውቆ ግዢ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ ያነሱት ብሩ (ዶ/ር)፣ ሁል ጊዜ ከውጪ መግዛቱ ሊያመጣ የሚችለውን ችግር በሚገባ ማጤን እንደሚያሻ አፅንዖት ሰጥተው ይናገራሉ።

ብሩ (ዶ/ር) እንደሰጡት ማብራሪያ ማዳበሪያን ሁል ጊዜ ከውጪ መግዛት፣ የዓለም ገበያ ከፍና ዝቅ ባለ ቁጥር ገበያው ላይ የሚፈጠረው የዋጋ ግሽበት ተጎጂ ያደርገናል። ኮሮና እንዲሁም የራሺያና ዩክሬን ጦርነት በዓለም ገበያ ላይ የፈጠረው ጫና የማዳበሪያ ዋጋን በሦስትና በአራት እጥፍ እንዲያድግ እንዳደረገው በማሳያነት ጠቅሰው እንዲህ ያሉ ክስተቶች ሲፈጠሩ ከውጪ ምንዛሪ አቅማችን ውስንነት ጋር ተዳምሮ ከኢኮኖሚ አኳያ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጎዳን ያስረዳሉ።

ብሩ (ዶ/ር)፣ የሞሮኮ መንግሥት ማዳበሪያ ለማምረት ድሬዳዋ ላይ የመሠረት ድንጋይ አስቀምጦ እንደነበር ጠቅሰው፣ መሟላት ያለባቸውን መሠረተ ልማቶች እየጠየቀ መዘግየቱን አስታውሰዋል። አያይዘውም፣ የግሉን ሴክተር ማሳተፉ ጥሩ አቅም የሚፈጥር መሆኑ እሙን ቢሆንም፣ መሠረተ ልማት ባልተሟላበት ሁኔታ ኢንዱስትሪዎችን የማቆም አቅምና ድፍረት ያለው መንግሥት ዘንድ በመሆኑ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ወደ ሥራው ቢገባ መልካም ነው ይላሉ።

ከባለሙያ አንጻርም በአሁኑ ሰዓት፣ ብዙ የኬሚካል ኢንጂነሮች አሉን ያሉት ተመራማሪው፣ ባለሙያዎቻችን ይህን መሥራት የሚያቅታቸው አይደሉም የሚል አስተያየት ይሰጣሉ።

እንደ ብሩ (ዶ/ር) አስተያየት፣ በአሁኑ ሰዓት በሀገራችን የእርሻ መሬት ከ18 ሚሊዮን ሄክታር አልፏል፣ የበጋ መስኖ ሲጨመርበት ደግሞ 20 ሚሊዮን ሄክታር ይደርሳል። እያንዳንዱ ሄክታር መሬት ላይ ሦስት ሦስት ኩንታል ማዳበሪያ ቢጨመርበት፣ ወደ ስልሳ ሚሊዮን ሄክታር በላይ ማዳበሪያ ይፈልጋል። እኛ እየገዛን ያለነው ደግሞ በዓመት 17 ሚሊዮን ቶን ማዳበሪያ ነው። ይህ ማለት መንግሥት መግዛት የሚችለውን ያህል እንጂ መሬታችን ወይም አርሶ አደሩ የሚፈልገውን ያህል ማዳበሪያ አይደለም ማለት ነው። ይህ የአቅርቦት ውስንነት ደግሞ ምርታማነታችን ውስን እንዲሆን ያስገድደዋል። ከግዢ ወጥተን ራሳችን ብናመርት ግን ምርታማነታችንን በከፍተኛ መጠን የማሳደግ አቅም እንፈጥራለን።

መሬታችንን የበለጠ በተጠቀምንበት መጠን የበለጠ እያረጀ፣ ለምነቱ እየቀነሰ የማዳበሪያ ፍላጎትም እየጨመረ መሄዱ የማይቀር ነው ያሉት ብሩ (ዶ/ር) ማዳበሪያን በራስ አቅም የማምረት ጉዳይ ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም የሚል አስተያየት ይሰጣሉ።

# ኢትዮጵያ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ዓመታዊ የአፈጻጸም ግምገማ መድረክ በቢሾፍቱ ከተማ ተካሂዷል።

በመድረኩ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የፕላንና ልማት ሚኒስቴር የአካባቢ፣ የአየር ንብረት እና የሥነ ሕዝብ ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ ሥዩም መኮንን እንደተናገሩት ኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥ ግንባር ቀደም ሆና ምላሽ በመስጠት በብዙ መንገድ የምትጠቀስ ቀዳሚ ሀገር ናት።

ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በርካታ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና እቅዶች አዘጋጅታ እየተገበረች መሆኑን ተናግረው በ2050 የካርቦን ልቀትን መጠን ዜሮ ለማድረግ እየሠራች መሆኑን ተናግረዋል።

የሰው ልጆች ለማደግና ለመለወጥ በሚያደርገው ጥረት ውስጥ ሰው ሠራሽ የሆኑ የሙቀት አማቂ ጋዞች መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ እያለ በመምጣቱ የአየር ንብረት ለውጥ ጫና ጉዳት እያደረሰ መምጣቱን የተናገሩት ሚኒስትር ዴኤታው በዚህ ምክንያት የአከባቢ መራቆት፣ የእንስሳትና የዕፅዋት ዝርያዎች መጥፋትና መመናመን፣ ሥነ ምሕዳሩ እየተጓደለ መምጣት እንዲሁም የዓለም ሙቀት እንዲጨምር በማድረግ ዓለምን እየተፈታተነ መምጣቱን ተናግረዋል።

የአየር ንብረት ለውጥ ተደጋጋሚ ድርቅ በማድረስ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን የምግብ ዋስትና ችግር እንዲገጥማቸው ማድረጉን ተናግረው የጐርፍ ተጋላጭነት መጨመሩን እንዲሁም ለውሃ እጥረት ምክንያት መሆኑንም አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ የጉዳዩን እጅግ አሳሳቢነት በመረዳት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር እየተገበረች መሆኑን አስታውሰው መርሐ ግብሩ የአከባቢ መራቆትን በመከላከልና ወደ አየር የሚለቀቀውን የሙቀት አምጪ ጋዞች በመቀነስ ትልቅ አስተዋፅዖ እንዳለው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ የደን ሽፋን እየጨመረ መምጣቱን ጠቁመው የተጀመረው የአየር ንብረት ለውጥን የመቀነስ አስተዋፅዖን እንደ ሀገር ተነሳሽነት በመውሰድ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ላይ በምትሠራቸው ሥራዎች ትልቁ የፋይናንስ ምንጭ መንግሥት እና የሀገር ውስጥ ሀብት መሆኑን የተናገሩት ሚኒስትር ዴኤታው በ2019 በተጠና ጥናት እስከአሁን በተደረገው እንቅስቃሴ 82 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ወጪ መደረጉን ገልጸዋል።

ከዚህ ውስጥ ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ምንጭ የተገኘው 0.03 በመቶ ብቻ መሆኑን ጠቁመው የብሔራዊ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በታቀደው እቅድ 316 ቢሊየን ዶላር እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

የእቅዱ 20 በመቶው በሀገር ውስጥ ፋይናንስ የሚሸፈን ሲሆን 80 በመቶ በዓለም አቀፍ ፋይናንስ እንደሚሸፈንም አመላክተዋል።

የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል የሚደረጉ እርምጃዎች በከፍተኛ ሁኔታ የፋይናንስ ድጋፍ የሚፈልጉ ናቸው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው የአየር ንብረት ለውጥ ላይ ኢትዮጵያ ማግኘት የሚገባትን ገንዘብ እያገኘች እንዳልሆነም ተናግረዋል።

የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ኢትዮጵያ ውስጥ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ እየሠሩ ያሉ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የመከታተል እና በየጊዜው የመገምገም ሥራ እንደሚሠራ ተናግረው በመድረኩ ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው ጊዜ ያቀዱትን ሥራ ምን ያህል እንዳሳኩ ግምገማ በማድረግ የጎደለውን ነገር በመመልከት ድጋፎች እንደሚደረግ ገልጸዋል።

ፕሮጀክቶቹ የተያዘላቸውን እቅድ በተያዘው ጊዜ ማጠናቀቅ መቻላቸው ሌሎች በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚሠሩ ፕሮጀክቶች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ያስችላል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ሥራዋን እውን ለማድረግ የሚያስችል አቅም የመፍጠር ፍላጎት ታሳቢ በማድረግ የሚሠራ ሥራ መሆኑንም ገልጸዋል።

በመድረኩ የአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚሠሩ 12 ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ቀርቦ ውይይት ተካሂዶበታል።

# ስተርጫ ከተማ የመጠጥ ውሃ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የተርጫ ከተማ የውሃ አገልግሎት ሥራ አስኪያጅ አቶ አብነት ቸርነትም የውሃ ችግር የከተማዋን ነዋሪ ያማረረ እንደነበር በማስታወስ፤ ለረጅም ጊዜ የነበረውን የመጠጥ ውሃ ያስቀራል ተብሎ የታመነበት የውሃ መሠረተ ልማት መገንባቱን ነው ያስታወቁት።

እንደ አቶ አብነት ከሆነ፤ ከዓለም ባንክ በተገኘ ብድር ከ268 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገበት የውሃ ፕሮጀክት ተገንብቷል። የምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ፕሮጀክቱን በማሠራት፣ የክትትልና ቁጥጥር ሥራውን ደግሞ የፌዴራል መንግሥት በመወጣት ፕሮጀክቱን ከዳር ማድረስ ተችሏል።

የተገነባው የውሃ መሠረተ ልማት ከ60 ሺ በላይ ዜጎችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ የጠቀሱት አቶ አብነት፤ የከተማዋ ነዋሪ በተጨማሪ በከተማዋ ዙሪያ የሚገኙ አጎራባች መንደሮችም ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ይገልጻሉ።

ፕሮጀክቱ በጊዜያዊነት አገልግሎት ቢጀምርም ያልተጠናቀቁ ሥራዎች በመኖራቸው የፕሮጀክት ርክክቡ ገና መሆኑን ነው ያስረዱት።

እንደ አቶ አብነት ማብራሪያ፤ በፕሮጀክቱ ውስጥ የተካተተው የ38 ኪሎሜትር የውሃ መስመር ዝርጋታ ሥራ እንደተጠናቀቀ የውሃ መስመሩን ወደ 10 መንደሮችን የማገናኘትና ግለሰቦችም የቆጣሪ አገልግሎት እንዲኖራቸው ተደርጓል። አዳዲስ ደንበኞችም በተራ እየተስተናገዱ ይገኛል።

በከተማዋና በዙሪያው በተለያዩ ኢንቨስትመንቶች ለተሠማሩ እንዲሁም ለጤናና ለትምህርት ተቋማት የውሃ አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግም ትኩረት መሰጠቱን አቶ አብነት ይገልጻሉ።

የተገነባው የውሃ መሠረተ ልማት የነበረውን ችግር ያስወግዳል ተብሎ ቢታሰብም ከተማዋ እያደገችና ኢንቨስትመንትም እየተስፋፋ ሲሄድ ችግሩ ተመልሶ እንዳይመጣ ልማቱን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባም ያስገነዝባሉ።

ለዚህም በአካባቢው ከሚገኙ ተፋሰሶችንና ምንጮችን ከአጋር አካላት ጋር በማልማት የውሃ አቅርቦቱን ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎች በ2017 ዓ.ም እንደሚከናወኑ ይጠቁማሉ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአፍሪካ ቀንድን ከትርምስ ወደ ትብብር የመለወጥ የኢትዮጵያ ውጤታማ መንገድ

የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ካለበት የጂኦ-ፖለቲካ ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ አኳያ፤ የበርካታ ኃይሎች ዓይን ማረፊያ ነው። በተለይ ቀጣናው ከቀይ ባሕር ጋር ካለው ቁርኝት፤ ብሎም በአካባቢው እንደ ኢትዮጵያ ዓይነት ከፍ ያለ የታሪክም፣ የፖለቲካና ሀገረ መንግሥት ውቅር ያላቸው ሀገራት ያሉበት መሆኑ ደግሞ፤ እነዚህ ኃይሎች በቀጣናው የራሳቸው ፍላጎት ለማስፈጸም ሲጥሩ እንዲኖሩ አድርጓል።

በዚህ ምክንያት የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ መረጋጋት ርቆት የጦርነት ቀጣና ሆኖ ዘልቋል። ትናንት እነ ሶማሊያ ሠላም ርቋቸው፤ ጠንካራ ሥርዓተ መንግሥት አጥተው ከሁለት አስርተ ዓመታት በላይ የመዝለቃቸው፤ ዛሬም እንደ ሱዳን ያሉ ሀገራት በሁለት ጎራ በተከፈለ የኃይል አሰላለፍ ውስጥ ገብተው በፈጠሩት ጦርነት ዜጎች ለስደትና ረሃብ፣ ብሎም ለከፋ እልቂት መዳረጋቸው፤ በጎረቤት ሀገራት መካከል ከመተባበር ይልቅ መጠራጠርን፣ ከመተባበር ይልቅ መገፋፋትን እንዲያስቀድሙ ሆነው እንዲሳሉ ያደረጋቸውም ይሄው ፍላጎት የወለደው የቀጥታም፣ የእጅ አዙር ተፅዕኖ ስለመሆኑ ብዙ ማረጋገጫ አለ።

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያም ከትናንት ጀምሮ ከፍ ያለ ዋጋ ከፍላለች። አሁንም ድረስ እየከፈለች ትገኛለች። ይሁን እንጂ፣ ኢትዮጵያ እንደ አንድ ነፃ እና ቅኝ እንዳልተገዛች ሉዓላዊት ሀገር በችግር ውስጥ ከመዳከር ይልቅ፤ ለራሷም፣ ለቀጣናውም የተሻለ ነገርን ከማሰብና ያሰበችውን ከመተግበር ወደኋላ ብላ አታውቅም። እናም ቀጣናውን ከመነጣጠል ወደ መተባበር፤ ከመጋጨት ወደ መወያየትና መደራደር፤ በድህነት ውስጥ ከመዳከር የጋራ አቅምን አሰባስቦ በጋራ ሠርቶ ወደ መበልጸግ ለማሸጋገር ከፍ ያለ ሥራን እያከናወነች ትገኛለች።

ይሄ ተግባሯ ደግሞ የቀጣናውን ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ኅብረት በ2063 አሳካዋለሁ ብሎ ያስቀመጠውን ግብ እውን እንዲያደርግ የሚያስችለው ነው። ለምሳሌ፣ ሠላምና ፀጥታ አንዱ የኅብረቱም፣ የኢትዮጵያም ትኩረት ነው። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የራሷን ሠላምና ደኅንነት ከማስጠበቅ ባሻገር፤ የጎረቤት ሀገራትን ሠላምና ደህንነት የሚያስጠብቁ ተግባራትን ስታከናውን ቆይታለች፤ እያከናወነችም ትገኛለች።

ለአብነትም፣ ትናንት በሶማሊያ እና ሱዳን ያለውን የሠላም ችግር ለማቃለል ሠራዊቷን በየአካባቢዎቹ አሰማርታ ለሠላማቸው ተግታለች፤ ዛሬም በዛው ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች። በሱዳን የተፈጠረውን ቀውስ ከመፍታት አኳያም ቀደም ሲል አደራድራ ሠላምን አውርዳለች፤ ዛሬም ያለውን ጦርነት ከማስቆም አኳያ በገለልተኝነት እየሠራች ትገኛለች።

ከልማትና አብሮ ከመበልጸግ አኳያም፣ ቀጣናውን በመሠረተ ልማት የማስተሳሰር ዓላማን ወጥና ከፍ ባለ ቁርጠኝነት እየተገበረች ትገኛለች። ከጎረቤት ሀገራት ጋር በየብስም በአየርም መሠረተ ልማት ተሳስራለች። በዚህም፣ ከጅቡቲ፣ ከኬንያ፣ ከሱዳንና ሌሎችም ጋር በተሽከርካሪም፣ በባቡርም፣ በአየርም የተሳሰረችባቸውን ሁነቶች መመልከት ይቻላል።

ከዚህ ባሻገር በንጹሕ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፤ በኤሌክትሪክ ኃይል ትስስር እና ሌሎችም ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው ከፍ ያሉ፤ የቀጣናውን አብሮነትና ትብብር በሚያጎለብቱ ጉዳዮች ላይ አተኩራ እየሠራች ትገኛለች። በቅርቡም የባሕር በር የማግኘት እና ቀጣናው ያለውን አቅም አዋጥቶ በጋራ መልማትና መበልፀግ የሚችልበትን አግባብ ነድፋ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ያደረገችበት ጉዳይም የዚሁ አንድ አካል ነው።

ከሰሞኑ የተሰማው፣ ከደቡብ ሱዳን ጋር ያለውን ትብብር ከፍ የሚያደርግ የመንገድ መሠረተ ልማት ትግበራን እውን የማድረግ አጀንዳም፤ የዚሁ ቀጣናውን የማስተባበር እና ከችግሩ የተሻገረ አሳቤና አቅም የማላበስ መንገዷ ማሳያ ነው። ይሄ ፕሮጀክት ኢትዮጵያ እና ደቡብ ሱዳንን የሚያገናኝ የ220 ኪሎ ሜትር መንገድ ግንባታን የሚመለከት ሲሆን፤ ይሄንን ፕሮጀክት እውን ለማድረግ በሁለቱ ሀገራት መካከል እ.አ.አ. ግንቦት 2023፣ የ738 ሚሊዮን ዶላር ስምምነት ተፈጽሞ ነበር። ከሰሞኑም፣ የደቡብ ሱዳን ብሔራዊ የሽግግር ሕግ አውጪ ምክር ቤት የዚህን ድንበር ተሻጋሪ መንገድ ግንባታ የገንዘብ ስምምነት አፅድቆታል።

ይሄን መሰሉ ርምጃ ደግሞ፣ የሁለቱ ሀገራት ትብብርና አብሮ የመልማት ፍላጎት መገለጫ ብቻ ሳይሆን፤ ኢትዮጵያ በቀጣናው እውን እንዲሆን የምትሻው የተባበረ እና በመተማመን ላይ የተመሠረተ የጋራ ብልጽፅግና እውን የመሆን መልካም ጅማሮ ነው።

ይሄ ደግሞ ኢትዮጵያ ቀጣናውን በሰው ኃይል አቅም እና በወታደራዊ ቁመና ግንባታ፣ በመሠረተ ልማት ትስስር፣ በሠላምና ደኅንነት እንዲሁም በዲፕሎማሲው መስክ አቅምን ደምሮ ቀጣናውን ከትርምስና ድኅነት ይልቅ፤ ወደ ትብብር፣ ሠላምና ብልጽግና የማሸጋገር መልካም እሳቤ ፍሬ እያፈራ ስለመሆኑ አመላካች ነው። ለአፍሪካ ኅብረት አጀንዳ መሳካትም መሠረት ነው!

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ክረምት ያፈራው አገልግሎት

በኃይሉ አበራ

መንግሥትና ሕዝብ የሚያከናውኗቸው ሥራዎች ተከትሎ እንደ ሀገር በምጣኔ ሀብትም ሆነ በማኅበራዊ ልማት በኩል ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎች ይታያል። በምጣኔ ሀብቱ በኩል ብዙ ለውጦች እየታዩ ናቸው። እነዚህ በግብርናው፣ በኢንዱስትሪው፣ በቱሪዝም ዘርፉ፣ ወዘተ እየተከናወኑ ያሉ ተግባሮች ለውጥም የበለጠ ለውጥ ለማምጣትም ትልቅ አቅም ናቸው። በማኅበራዊው መስክም ስንመለከት በትምህርት፣ በጤናና በመሳሰሉት ሰፋፊ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

በአንጻሩ ሀገሪቱ ብዙ የመልማት ፍላጎትና አቅም ቢኖራትም በተለያዩ ችግሮች ሳቢያ እና በአቅም ውስንነት ሳቢያ ልትፈታቸው ያልቻለቻቸው በርካታ ችግሮችም አሉባት። እነዚህን ችግሮችም አልገፋቻቸውም፤ ችግሮቹን ዜጎች በተለያየ አግባብ ለመፍታት እንዲንቀሳቀሱም ለማድረግም እየሠራች ትገኛለች።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎትም ከእዚህ አኳያ ይጠቀሳል። ይህ የመደጋገፍ እሴት በተለይ በክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እየሰፋ መጥቷል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአዲስ አበባ በመኖሪያ ቤት እድሳትና አዲስ መኖሪያ ቤት ግንባታ፣ በማዕድ ማጋራት፣ በደም ልገሳ የተከናወኑት ተግባሮች የኢትዮጵያውያንን የመደጋገፍ እሴት ፍንትው አርገው አሳይተዋል። በእዚህ ቅዱስ ተግባር የሀገሪቱን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን (ዶ/ር) ጨምሮ በርካታ የመንግሥት ባለሥልጣናት እየተሳፉበት ይገኛሉ።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፣ ባለሀብቶች እንዲሁም በርካታ ግለሰቦችንም እያሳተፈ ይበልጥ ውጤታማ እየሆነ የመጣው ይህ ተግባር በየጊዜው እያደገ እና እየሰፋ ሀገራዊ መልክ እየያዘም ይገኛል። በአገልግሎቱ እየተከናወነ ያለው ተግባር በገንዘብ ሲተመን በብዙ ቢሊዮኖች ብር እየተገመተ ይገኛል። ይህም ኢትዮጵያውያን ከተባበሩ በውስብስብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ሕይወት የመንግሥት እጅ ሳይጠበቅ መታደግ እንደሚችል ትልቅ ማሳያ ነው።

በተያዘው 2016 በክረምት ወራት በሚደረገው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ብቻ ከ21 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት ሥራ እንደሚሠራ ተጠቁሟል፤ በዚህ አገልግሎት ከ40 ሚሊዮን ሰዎች በላይ የሚሳተፉበት ሲሆን፤ በአገልግሎቱ ያላቸው በገንዘብ፣ የሌላቸው ደግሞ በጉልበታቸውና በእውቀታቸው ይሳተፉበታል። በዚህ አገልግሎት ከ50 ሚሊዮን ሰዎች በላይ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ መረጃዎች ጠቁመዋል።

መምህራን በማስተማር፣ የጤና ባለሙያውም የሕክምና አገልግሎት በመስጠት፣ የብዙኃን መገናኛ ባለሙያዎችም እንዲሁ መረጃ በማድረስና በመሳሰሉት ይሳተፉበታል። ተማሪዎች ባላቸው እውቀትና ጉልበት በአገልግሎቱ በስፋት ይሰማራሉ። ሕዝቡን በሚገባ ማነቃነቅ ከተቻለ ለእዚህ አገልግሎት፣ አገልግሎት መስጠት የማይችል አንድም ዜጋ አይኖርም ማለት ይቻላል።

ከዚህ ሁሉ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ ምን ያህል ትልቅ አቅም እንዳለው መገንዘብ አያዳግትም። በአገልግሎቱ ብዙ ሚሊዮን ሰዎችን ከልጅ እስከ አዋቂ ማንቀሳቀስ፣ ብዙ ቢሊዮን ብር የሚገመቱ አያሌ ሥራዎች የሚሠሩበት እንዲሁም ብዙ ሚሊዮን ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ በእርግጥም በሀገሪቱ መረዳዳት ከተቻለ አያሌ ዜጎችን መታደግ የሚያስችል አቅም እንዳለ ያመለክታል።

በእዚህ ታላቅ ሥራ ዜጎችን መርዳት ብቻ ሳይሆን የመንግሥትን ሸክም ማቃለል እንደሚቻልም ማየት ተችሏል። ሕዝብና ሀገር በእጅጉ የሚፈልጓቸው አያሌ ሥራዎች ላሉበት የኢትዮጵያ መንግሥት ሕዝቡ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ይህን ያህል ሥራ መሠራት መቻሉ ትልቅ አቅም መሆኑን ማየት ያስቻለም ነው።

በተለምዶ ሕዝብ የጎደለውን ሁሉ መንግሥት እንዲሞላ ሲጠበቅ ኖሯል። የሕዝቡን ጉድለት በራሱ በሕዝቡ መሙላት እንደሚቻል በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማሳየት መቻል በራሱ ትልቅ ተግባር ነው። ለእዚህም በእዚህ ተግባር ዘለው የገቡትንም ሆነ በማስተባበሩ ሥራ ለተሠማሩትና ምቹ ሁኔታ ለፈጠረው መንግሥት ትልቅ ምስጋና ይገባቸዋል።

የኢትዮጵያውያን የመረዳዳት እሴት ይበልጥ እንዲጠናከር የተደረገበትም ነው፤ ከሀገራችን ሕዝብ 98 በመቶ ያህሉ ሃይማኖተኛ እንደሆነ ይገለጻል። የየእምነቱ ተከታይ ዜጎችም በእምነቱ እሴቶች የተገነባ ነው። ሕዝቡ በባሕልም በኩል ቢታይ እንዲሁ መረዳዳት ትልቅ እሴት አርጎ የኖረ ነው። በጎነት የኢትዮጵያዊነት መገለጫም ነው፤ አንድ ኢትዮጵያዊ ሌላውን ኢትዮጵያዊ በበጎነት ሲያስብ እምነቱን ተመልክቶ አይደለም፤ ኢትዮጵያዊነቱን፣ ወገኑ መሆኑን ተመልክቶ ነው። ይህ ሁሉ ኢትዮጵያ ያለውን የሚያካፍል፣ መረዳዳትን ባሕሉ ያደረገ ሕዝብ ሀገር መሆኗን ያስገነዝባል።

ይህ የኢትዮጵያውያን የመረዳዳትና መደጋገፍ ባሕል ግን በቀደመው ልክ አለ ብሎ መናገር የማያስችሉ ሁኔታዎች እየታዩ ናቸው። በዜጎች ርብርብ ከችግር ሊወጡ የሚችሉ አካል ጉዳተኞች፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች፣ የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ የአዕምሮ ሕመሙን፣ .ወዘተ ቁጥር እየጨመረ መምጣት የመደጋገፍ እሴቱን በቀደመ ቁመናው ላይ ነው ለማለት የማያስችል ሆኖ ቆይቷል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እነዚህን የኅብረተሰብ ክፍሎች ለመታደግ በበጎ ፈቃድ አገልግሎትና በመሳሰሉት እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ዜጎች በስፋት እየተሳፉ መሆናቸው፣ ኢትዮጵያውያን ዘመናትን በዘለቀው የመረዳዳት ባሕላቸው ላይ አርፎ የነበረውን ትቢያ በማራገፍ በተናጠል ከሚያደርጉት ዜጎችን የመታደግ ጥረት ወደ ተቀናጀ ርብርብ በመግባት ለውጥ ማሳየት መጀመራቸውን ያመለክታል።

የርብርቡ አንድ ማሳያም ሰሞኑን በይፋ የተጀመረው የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ነው። እንደሚታወቀው የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በተለይ በአዲስ አበባ በስፋት ሲካሄድ ቆይቷል፤ በዚህም ዜጎችን ተጠቃሚ ያደረጉ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል።

ዘንድሮም ይህን አገልግሎት ይበልጥ እንደ ሀገር ማስፋት የሚያስችል የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ነው በመላ ሀገሪቱ ማካሄድ ውስጥ የተገባው። ተማሪዎችን በማሳተፍ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ መሆን የጀመረው አገልግሎት በዘንድሮው ንቅናቄው ወጣቶች ብቻ አይደሉም የሚሳተፉበት። ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲሳተፍበት ይደረጋል። ይህም ሰፊ ሀገራዊ ፋይዳ ይኖረዋል።

የበጎነት ሥራ የአንድ ተቋም ወይም የብዙ ተቋማት ሥራ ሳይሆን ሁሉም የራሱን ድርሻ የሚወስድበት ነው። ለአንድ አቅመ ደካማ እናት የሚታደሰው ቤት የኢትዮጵያውያንን ቤት የመጠገን አንዱ አካል በማድረግ የሚከናወን ተደርጎ እየታየ ነው። ተቋማዊ በሆነ መንገድ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱን በመላ ሀገሪቷ ተደራሽ የሚደረግበት ሁኔታ እየታየ ነው። የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ ሀገራዊ ንቅናቄ ሀገርን የመገንባት አንዱ አካል እንጂ የአንድ፣ የሁለት፣ ወዘተ ጊዜ ወይም የዘመቻ ሥራ ብቻ እንደማይሆንም ብዙዎች ይስማሙበታል።

በአገልግሎቱ ዘንድሮ በተለይ በተማሪዎች የሚከናወኑ ተግባሮች ለዜጎችም ለሀገርም ወሳኝ ናቸው። የአቅመ ደካሞችን መኖሪያ ቤት ማደስ ወይም በአዲስ መልክ መሠራት፣ ተማሪዎችን ለመጪው የትምህርት ዘመን ማዘጋጀት፣ ወዘተ ማከናወን ብቻ አይደለም ራሳቸውንም የሚገነቡበት ሁኔታ ይፈጠራል። ተማሪዎች በወሰን ተሻጋሪ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ ከ20 ሺ በላይ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለአንድ ወር ቆይታ ያደርጋሉ። በዚህም ከሚሰጡት አገልግሎት በተጨማሪ ራሳቸውም ከሚቆዩበት ማኅበረሰብ ብዙ የሚወስዱት ይኖራቸዋል ተብሎ ታሳቢ ተደርጓል።

ተማሪው ሀገር ውስጥ ያለውን እምቅ አቅም መረዳት ይችላል፤ የሌላውን ባሕል እና ቋንቋ፣ አኗኗር የሚያውቅበት ምቹ ሁኔታ ይፈጠርለታል። የሀገሪቱን ችግሮች እና ፈተናዎች፣ መልካም ዕድሎች መመልከትም ይችላል። አገልግሎቱን አጠናቆ ሲመለስ ጥሩና ሥራ ፈጣሪ ዜጋ እንደሚመለስ ይጠበቃል። ከሌሎች የማኅበረሰቡ አካላት ጋር በመገናኘቱም የሰከነ፣ ያደገ፣ የሠለጠነ ግንኙነት ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል። ይህ ሁሉ ደግሞ ወጣቱን በተለያዩ መልኩ ለመገንባት ለሚደረገው ጥረት ትልቅ አቅም ሆኖ ያገለግላል።

ይህ አገልግሎት ነው እንግዲህ በክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተዘርቶ በክረምት ሰፋፊ ሥራዎች ከማከናወንም አልፎ ሥራው በበጋ ጭምር እንዲቀጥል እየተደረገ ያለው። ይህ ለአቅመ ደካሞች፣ የጤና መታወክ ለደረሰባቸው ወገኖች፣ ለጎዳና ተዳዳሪዎች፣ ለተማሪዎች፣ በአጠቃላይ ለዜጎችና ለሀገር መድኅን እየሆነ የመጣ አገልግሎት የበለጠ ስር እየሰደደ እንዲመጣና የሕዝብና የሀገር አለኝታነቱን እንዲወጣ ለማድረግ ብዙ መሥራት ያስፈልጋል። ካለው ችግር ብዛት፣ ችግሩን ለመፍታት ካለው ሰፊ አቅም አኳያ ሲታይ አሁን እየተሰጠ ያለው አገልግሎት ይበልጥ እንዲሰፋ መሥራት ያስፈልጋል፤ ለእዚህ ደግሞ በማስተባበሩ ሥራ ላይ የተሰማሩ ተቋማት፣ ግለሰቦች፣ ወዘተ ሰፊ ሥራ ይጠብቃቸዋል።

# ነፃ ሃሳብ

# የኮሪደር ልማት ትሩፋቶችን መንከባከብ የሁሉም ኃላፊነት ነው

**ጋሹ ደግዛው (ከወሎ ሠፈር)**

መዲናችንን አዲስ አበባ ከተማን ጨምሮ ሌሎች ከተሞቻችንን ጽዱና ማራኪ ሆነው ማየትን ማንኛውም ሰው የሚጠላ አይመስለኝም። ሁሉም ከተሞች ጽዱና ማራኪ እንዲሆኑ ደግሞ ከመንግስት ባሻገር የሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ድጋፍና ትብብር ያስፈልጋል። ስለ ሌሎች ከተሞች የኮሪደር ልማት እንቅስቃሴ ባለውቅም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሪደር ልማት እንቅስቃሴ ሕዝቡ የሚያደርገው ድጋፍና ትብብር የጎላ በመሆኑ እየተሠሩ ካሉት የኮሪደር ልማቶች መካከል አብዘኛዎቹ በአጭር ጊዜ ተጠናቀው ለአገልግሎት ክፍት ሆነዋል።

ስለ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶች እንቅስቃሴ በመገናኛ ብዙሃን ከምንሰማውና ከምናየው በተጨማሪ ውበና ማራኪ ሆነው የተሠሩ ለመሆናቸው በዓይናችን እያየን ስለሆነ ሌላ ምስክር አያስፈልገንም። ከተጀመሩት የኮሪደር ልማት ስራዎች መካከልም የተወሰኑት ተጠናቀው ለመኪና፣ ለብስክሌት እና ለእግረኛ ክፍት መሆናቸው የኮሪደር ልማቱ ፍሬ እያፈራ ስለመሆኑ ማሳያ ነው።

የተጠናቀቁት የኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶች በቀን 8 ሰዓት ብቻ በመሥራት የተጠናቀቁ ሳይሆን 24 ሰዓት በመሥራት የተጠናቀቁ ስለመሆናቸው በመገናኛ ብዙሃን ከምንሰማው ባሻገር የኮሪደር ልማቶቹ በሚሠሩባቸው አካባቢዎች የምንኖር ሰዎች ያለውን እንቅስቃሴ በዓይናችን እናያለን፤ ሌሊቱን ሙሉ ሲሠራም የማሽኖችን እና የሰዎችን እንቅስቃሴ በጆሯች እንሰማለን። በአገራችን 24 ሰዓት መሥራት መጀመሩ ደግሞ የሥራ ባህልን እየተለወጠ ስለመሆኑ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል።

የኮሪደር ልማቶቹ 24 ሰዓት መሠራታቸውም ብዙ ጠቀሜታዎችን ይዞ መጥቷል፤ ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው ጊዜ እና በጀት በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቁ ከማድረጉ ባሻገር ለብዙዎች የስራ ዕድል መፍጠር ችሏል። ሥራው በአጭር ጊዜ መጠናቀቅም ሕዝቡ ከልማቱ እንዲጠቀም ያደርጋል። ለብዙ ሰዎች የሥራ ዕድል እየፈጠረ ነው ሲባልም በፕሮጀክቶቹ ተቀጥረው ለሚሠሩት ብቻ ሳይሆን በግል ሥራ የተሠማሩ ሰዎችም ሌሊት ለሚሠሩ ሠራተኞች የምግብ እና ሻይ ቡና አገልግሎት ስለሚሰጡ ከፕሮጀክቱ ውጭ ላሉ ሰዎችም የሥራ ዕድል እየፈጠረ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜና በጀት መጠናቀቅም ጠቀሜታው ለመንግሥትና ለሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለሥራ ተቋራጭ ድርጅቶችም ጭምር ነው። ምክንያቱም የፕሮጀክቱ የመሥሪያ ጊዜ ባጠረ ቁጥር የሥራ ተቋራጮች አንድን ፕሮጀክት ለመሥራት ሲዋዋሉ የተመኑት ዋጋ ባለበት ስለሚቆይ ከኪሳራ ያድናቸዋል። ስለዚህ የተጀመረው የኮሪደር ልማት ብዙ ተሞክሮዎችን እያለማመደ ይመስለኛል። የኮሪደር ልማቱ በርካታ ቤቶች ቢፈርሱም ሰዎች ከለመዱበት አካባቢ ለቀው በመሄዳቸውና በዚህ ምክንያት አንዳንድ ማህበራዊ መስተጋብሮች ስለቀረባቸው ቅር ከመሰኘታቸው በስተቀር አንድም የልማት ተነሺ ከሞቀ ቤቴ ወጥቼ ሜዳ ላይ ወደቅኩ የሚል ቅሬታ ባለመንሳቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አመራሮች ሊመሰገኑ ይገባል፡፡

**በካፌዎችና በሬስቶራንቶች ሻይ ቡና እያሉ መዝናናት ለሚፈልጉ ሰዎችም በየመንገዱ ዳር በተከፈቱ ካፌዎችና በሬስቶራንቶች አረፍ ብለው ለመዝናናትም ጥሩ አጋጣሚ ተፈጥሮላቸዋል**

የመኪና፣ የብስክሌት እና የእግረኛ መንገዶች በየራሳቸው መስመር መሠራታቸውም መኪናዎች፣ ብስክሌቶች እና እግረኞች በትክክል የራሳቸውን መንገድ ጠብቀው እንዲጓዙ ምቹ ሁኔታን ስለፈጠረ እግረኞች እና ብስክሌቶች ከመኪና ጋር እየተገፋፉ መሄዳቸውንም ያስቀራል። የመኪና፣ የብስክሌትና የእግረኛ መንገዶች የየራሳቸውን መስመር ጠብቀው ከመሠራታቸው በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች የውስጥ ለውስጥ መንገዶች እና የመሻጋገሪያ ድልድዮች በመሠራታቸው እነዚህ ሁሉ ተደማምረው ለትራፊክ አደጋ መቀነስም አስተዋፅዖ የሚኖራቸው ይሆናል፡፡

የመኪና፣ የብስክሌትና የእግረኛ መንገዶች እንዲሁም የውስጥ ለውስጥ መንገዶችና የመሻጋገሪያ ድልድዮች መሠራታቸው ብቻ ግን የትራፊክ አደጋን ይቀንሳል የሚል እምነት የለኝም። ምክንያቱም መኪናዎች፣ ብስክሌቶችና እግረኞች የየራሳቸውን መስመር ጠብቀው ካልሄዱ እንዲሁም የተሠሩትን የውስጥ ለውስጥ መንገዶችና የመሻጋገሪያ ድልድዮችን በአግባቡ ካልተጠቀሙባቸው ችግሩን ስለማይቀርፍ። የመኪና አሽከርካሪዎች፣ በብስክሌትና በእግረኛ መንገዶች የሚያሽከረክሩ ከሆነ ለረጅም ዓመት እንዲያገለግሉ ታስበው የተሠሩ መንገዶች ዕደሜያቸው ያጥራል፤ እግረኛና ብስክሌቶች በመኪና መንገድ የሚሄዱ ከሆነም ለትራፊክ አደጋ መንስኤ መሆናቸው አይቀርም፡፡

ይህን የምለው እንዲሁ ከመሬት ተነስቼ አይደለም። በእግረኛ እና በብስክሌት መንገዶች መኪና ሲነዳበት፣ በመኪና በብስክሌት መንገዶች እግረኛ ሲሄድበት፣ በመኪና እና በእግረኛ መንገዶች ብስክሌት ሲጋለብበት ስለተመለከትኩ ነው። የሞተር ብስክሌቶች ነገር ደግሞ እጅግ በጣም የከፋ ነው። መኪና በመብራት ምክንያት ቆሞ እያዩ እነሱ ሹልክ ብለው ስለሚገቡ ለትራፊክ አደጋ ስጋት መሆናቸውን ሁሌ እታዘባለሁ። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚመለከታቸው አካላት ቀድመው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት የሚኖርባቸው ሲሆን ከግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቱ በኋላ መንገዶችን በሥርዓቱ በማይጠቀሙት ላይ እርምጃ መውሰድም ስለሚያስፈልግ የሚመለከታቸው አካላት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት መወጣት አለባቸው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

የኮሪደር ልማቱ በተሠራባቸው አካባቢዎች ለዓይን ማራኪ የሆኑ አበባዎች እና አረንጓዴ ተክሎች መኖራቸውም ሰዎች ሲጓዙ ቆይተው በሚደክማቸው ጊዜ ውብ አበባዎችንና አረንጓዴ ተክሎችን እየተመለከቱ ማረፍ እንዲችሉም ዕድል ይሰጣቸዋል። ሕፃናት ልጆቻቸውን ይዘው የሚጓዙ ወላጆችም ሕፃናቱ የሚጫወቱበት ቦታ ስለሚያገኙ ያለምንም ጭንቀት አረፍ ብለው ትንፋሽ እንዲወስዱ ይረዳቸዋል። በኮሪደር ልማቱ አካባቢ የሚገኙ ሕንፃዎች፣ የመንገድ መብራቶች እና የመሳሰሉት እየታደሱ መሆናቸውም የኮሪደር ልማቱ ሲጠናቀቅ ለአዲስ አበባ ከተማ ተጨማሪ ውበት የሚፈጥሩ ናቸው፡፡

በካፌዎችና በሬስቶራንቶች ሻይ ቡና እያሉ መዝናናት ለሚፈልጉ ሰዎችም በየመንገዱ ዳር በተከፈቱ ካፌዎችና በሬስቶራንቶች አረፍ ብለው ለመዝናናትም ጥሩ አጋጣሚ ተፈጥሮላቸዋል። የኮሪደር ልማቱ በተጠናቀቀባቸው በአራት ኪሎና በፒያሳ አካባቢ በየመንገዱ ዳር በተከፈቱ ካፌዎችና ሬስቶራንቶች ሰዎች ሻይ ቡና ሲሉም ተመልክቻለሁ።

በሌላ በኩል የሰው ልጅ እንደሌሎች እንስሳት በደመ ነፍስ የሚንቀሳቀስ ሳይሆን የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች አስቦና አልሞ የሚተገብር ቢሆንም ቸልተኛ ሰዎችን ሳይጨምር በከተሞች አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች መንገድ ላይ ሲሄዱ በሚገጥማቸው ሕመም አለያም ተፈጥሮ አስገድዷቸው መቋቋም ሲያቅታቸው መንገድ ላይ ስለሚፀዳዱ (ሽንታቸውን ስለሚሸኑ) ከተሞችን ያቆሽሻሉ፡፡

መንግሥት ይህን ተገንዝቦ ይመስለኛል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚሠሩ የኮሪደር ልማቶች በተለያዩ አካባቢዎች 120 ዘመናዊ የመፀዳጃ ቤቶችን አካቶ ለመሥራት ያቀደው። እነዚህ ዘመናዊ መፀዳጃ ቤቶች መሠራታቸው የአዲስ አበባ ከተማ ጽዳት ለመጠበቅ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ የሚል ተስፋ ቢኖረኝም ትክክለኛ የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀም ካልኖረ የመፀዳጃ ቤቶቹ መሠራት ብቻ የከተማዋን ጽዳት ይጠብቃል የሚል እምነት የለኝም። ምክንያቱም የመፀዳጃ ቤቶቹ አጠቃቀም እና አያያዝ ችግር ካለባቸው ለከተማይቱ ፅዳት መጓደል የባሰ መንስኤ እንዳይሆንም ሥጋት ስላለኝ መፀዳጃ ቤቶቹን የሚያስተዳድሯቸው አካላት እና እያንዳንዱ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ መፀዳጃ ቤቶቹን በአግባቡ ለመጠቀምና ለመያዝ ኃላፊነቱን በመወጣት ድጋፍና ትብብር ማድረግም ይጠበቅበታል።

ከዚህ ቀደም በመንግሥት ቁጥጥር ሲደረግባቸው የነበሩ የአዲስ አበባ ከተማ የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች አሁን ካሉት የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች በአንፃራዊነት ጽዱ ነበሩ ማለት ይቻላል። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ጥቅም እየሰጡ ያሉ የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች ሕመም ወይም ተፈጥሮ ስለሚያስገድድ እንጠቀምባቸዋለን እንጂ ንፅህናቸው በጣም የወረደ መሆኑ እሙን ነው። መፀዳጃ ቤቶችን የሚያስተዳደሩት አካላትም ከተጠቃሚው ገንዘብ ይሰበስባሉ እንጂ ስለንፅሕናቸው ሲጨነቁ አይስተዋልምና ሊታሰብበት ይገባል።

በኮሪደር ልማቱ የሚሠሩ መፀዳጃ ቤቶችን ንፅህና ለመጠበቅ መፀዳጃ ቤቶችን ከሚያስተዳድሩ አካላት እና ከእያንዳንዱ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ትልቅ ኃላፊነት የሚጠበቅ ይመስለኛል። እያንዳንዱ ዜጋ መፀዳጃ ቤቶችን በአግባቡ የማይጠቀምባቸውና በንጽህና የማይያዛቸው ከሆነ ግን ከጥቅሙ ጉዳቱ እንዳያመዝን ስጋት አለኝ።

ሁሉንም መሠረተ ልማቶች አካቶ የሚሰራው የኮሪደር ልማት ከዳር ደርሶ እያንዳንዱ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪን ተጠቃሚ እንዲያደርግ ከተፈለገ መንግሥት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ዜጋ ድጋፍና ትብብር ያስፈልጋል። መንግሥት የሕዝብ ወኪል በመሆኑ ሕዝብን ወክሎ ሥራዎችን ይሠራል እንጂ ብቻውን የሚያደርገው አንዳችም ነገር አለመኖሩን ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ሊገነዘብ ይገባል።

መንግሥት ሕዝብን ወክሎ የሚሠራውን ፕሮጀክቶች ሕዝብ ኃላፊነት ወስዶ ካልተንከባከበና በአግባቡ ካልተጠቀመ የአገልግሎት ጊዜያቸው ሊያጥር፤ አለያም ምንም አገልግሎት ሳይሰጡ ከጥቅም ውጭ ሊሆን ስለሚችል የሁሉንም ኅብረተሰብ ኃላፊነት ይጠይቃል። ለሕዝብ ጥቅም ተብለው ብዙ ሀብት የፈሰሰባቸው ፕሮጀክቶች አንዳንዴ በሕዝቡ የተሳሳተ ግንዛቤ፤ ሌላ ጊዜ በመንግሥት አስፈጻሚ አካላት የአፈጻጸም ችግር ሕዝቡን ሳይጠቅሙ መና የሚቀሩበት አጋጣሚዎች ብዙ ናቸውና ከፕሮጀክት ሥራዎች ጎን ለጎን በመገናኛ ብዙሃን በኩል ወይም በተቋማቱ የተግባቦት ክፍል የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በመስጠት የልማቱን ትሩፋቶች መንከባከብ ያስፈልጋል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የቴክኖሎጂና የፈጠራ ውጤቶች - በቴክኒክና ሙያ ተቋማት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

እንደሀገር ችግር ፈቺና ተኪ የሆኑ የቴክኖሎጂና የፈጠራ ውጤቶች በማፍለቅ ረገድ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የማይተካ ሚና አላቸው። ተቋማቱ የሰለጠነ ብቁ የሰው ኃይል ከማፍራት ባሻገር የኅብረተሰቡን ችግር ሊቀርፉ የሚችሉ የቴክኖሎጂና የፈጠራ ውጤቶች በመስራት ለኅብረተሰቡ እያበረከቱ ይገኛሉ። እነዚህ ስራዎችም ኅብረተሰቡ እንዲያውቅ እና እንዲጠቀምበት ለማድረግ በየዓመቱ በሚዘጋጅ አውደርዕይ ላይ ለእይታ ያቀርባሉ።

በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ያሉ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት በየዓመቱ ሥራቸውን የሚያቀርቡበት የቴክኒክና ሙያ ሳምንት ይካሄዳል። ዘንድሮም 14ኛው ከተማ አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሳምንት ከሰኔ 15 እስከ 20 ድረስ ተካሂዷል። በአውደርዕዩ በርካታ የቴክኖሎጂና የፈጠራ ውጤቶች የቀረቡ ሲሆን ሥራዎቹ ተባዝተው የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያግዙና ተኪ ምርቶችን በስፋት ለማምረት ተነሳሽነትን የሚፈጥሩ እንደሆኑ ታምኖባቸዋል። ይህም ኅብረተሰቡ የተሰሩ ሥራዎችን በመገንዘብ እንዲጠቀም ለማድረግ ያስችላል።

በከተማው የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሰራቸውን ሥራዎች በአውደ ርዕዩ ይዘው ቀርበዋል። ከእነዚህ መካከል የአቃቂ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ አንዱ የአውደርዕዩ ተሳታፊ ነው። ኮሌጁ ለእንስሳት መኖ ማቀናበሪያ የሚውል ፐሌት ማሽን ሰርቷል። አቶ አበራ ደሳለኝ አቃቂ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የቴክኖሎጂ ባለሙያ ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፤ ኮሌጁ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሚሰራው ኢንተርፕራይዞች ያቀረቡትን ፍላጎት መነሻ አድርጎ ነው። የእንስሳት መኖ ማቀናበሪያ ማሽንም አንድ ኢንተርፕራይዝ ባቀረበው ፍላጎት መሠረት ተደርጎ የተሰራ ነው "አንድ ኢንተርፕራይዝ እንደዚህ አይነት ቴክኖሎጂ ቢሰራልኝ በዚህ ሰርቼ ሀብት ማፍራት እችላለሁ በሚል ይህንን ቴክኖሎጂ እንድንሰራለት ስለጠየቀን ይህንኑ መነሻ በማድረግ ዲዛይን በመስራት በዚህ መልኩ ተሰርቷል። ፍላጎቱን ያቀረበው ኢንተርፕራይዝ የተሰራውን ማሽን ካየ በኋላ የራሱን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ዲዛይን ሊጨምርም ሆነ መጠኑን በማሳነስ ወይም በማተለቅ ሊጠቀምበት ይችላል" ይላሉ።

ማሽኑ ከተለያዩ ትምህርት ክፍል በተውጣጡ ስድስት አሰልጣኞች የተሰራ መሆኑን ይናገራሉ። የእንስሳት መኖ ማቀናበሪያ ማሽኑ ለዶሮ፣ ለከብቶችና ለጋማ ከብቶች መኖ ማቀናበሪያነት የሚውል ሲሆን ፍላጎቱን ያቀረበው ኢንተርፕራይዝ ብቻ የሚጠቀምበት ሳይሆን፤ ሌሎችም ማሽኑን የሚፈልጉና የሚጠይቁ ኢንተርፕራይዞችም ሆነ ኅብረተሰቡ ሊጠቀምበት የሚችል የቴክኖሎጂ ውጤት ነው ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ማሽኑ ከውጭ ከሚመጣው ጋር በዲዛይን ይለያያል፤ ከውጭ የሚገባው የመኖ ማቀናበሪያ ማሽን የተያያዘና አንድ ላይ ያለ ሲሆን፤ ይሄኛው ግን ሁለቱንም በአንድ ላይ የሚያገናኝ መሳሪያ የተገጠመለት ነው። ሁለቱንም የሚያገናኝ መሳሪያ መገጠሙ በሰው ኃይል ከአንዱ ወደ አንዱ ማሽን የሚደረገውን ሂደት በማስቀረት ማሽኑ በራሱ ፕሮሰስ እንዲያደርግ ያግዛል። ይህ ማሽኑ ከውጭ ከሚገባ የተሻለ እንዲሆን ያደርጋል።

ማሽኑ ከውጭ ከሚገባው ጋር ሲነጻጸር በዋጋ ተመጣጣኝ እንዲሆን ተደርጎ የተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከውጭ የሚገባው በገበያ ላይ እስከ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ዋጋ ያለው ሲሆን በሀገር ውስጥ የተሰራው አዲሱ ማሽን ግን 580 ሺ ብር እንደፈጀ ይናገራሉ።

ማሽኑ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰራ ነው የሚሉት አሰልጣኙ፤ በቀጣይ በሶላር እና በኤሌክትሪክ ኃይል እንዲሰራ በማድረግ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጎ እንደሚሻሻል ይናገራሉ። ማሽኑን ለመስራት ጥቅም ላይ የዋሉት ቁሳቁሶች፤ አብዛኛው ላሜራዎች እንደሆኑም ገልጸዋል።

እንደአሰልጣኙ ማብራሪያ፤ የእንስሳት መኖ ማቀናበሪያ ማሽኑ የተለያየ ለእንስሳት በግብዓትነት የሚውሉት እንስሳት መመገብ የሚችሏቸው መኖ አይነቶች ማዘጋጀት ያስችላል። የዶሮ መኖ ለማዘጋጀትም ፍሩሽካ ከተለያዩ ነገሮች ጋር በማቀላቀል ማዘጋጀት የሚያስችል ነው። በተጨማሪም የዶሮ ኩስን ከመኖ ጋር አቀላቅሎ ያዘጋጃል። ማሽኑ በሦስት ደቂቃ አንድ ኪሎ ግራም መኖ ያመርታል።



የእንሰሳት መኖ ማቀናበሪያ ማሽን

ማሽኑ አገልግሎት ላይ ውሎ ፍተሻ ተደርጎ ሀሳቡን ያቀረበው ኢንተርፕራይዝ አይቶ የወደደው ስለሆነ አሁን አውደርዕይ ላይ እንዲቀርብ የተደረገበት ዋና ምክንያት ኅብረተሰቡ አይቶት እንዲጠቀምበት ታስቦ መሆኑን ያመላክታሉ። በአሁኑ ወቅት ማሽኑ ለኢንተርፕራይዝ የተላለፈ በመሆኑ ኮሌጁም ሰነዱን ለኢንተርፕራይዝ የሚያስተላልፍ መሆኑን ያስረዳሉ። ኢንተርፕራይዙ ዲዛይን ለመጨመር ሆነ ሌሎች የድጋፍ አገልግሎት ሲያስፈልገው ኮሌጁ አስፈላጊው ድጋፍና እገዛ እንደሚያደርግለት ነው ያስረዱት።

ይህ የመኖ ማቀናበሪያ ማሽን ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰራ ቢሆንም ጥራቱን የጠበቀ ነው ያሉት አሰልጣኙ፤ ይህ ማሽን በድጋሚ ቢሰራ ደግሞ ከዚህ በበለጠ እንዲሻሻል ተደርጎ መስራት የሚችል መሆኑን ይገልጻሉ። ማሽኑን በአውደርዕዩ የተመለከቱት አብዛኞቹ ሰዎች ወደውታል እንዲሰራላቸው የፈለጉም በርካቶች እንደሆኑ ጠቅሰው፤ በተለይ ከብቶች እያደለቡ ያሉ ሰዎች ማሽኑን እንደሚፈልጉት ይናገራል። "በቀጣይም ከኅብረተሰቡ የተሰጡት አስተያየቶች በመሰብሰብ የተሻለ ስራ ሰርተን እናሳያለን "ብለዋል።

ሌላኛው የአውደርዕዩ ተሳታፊ የምስራቅ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ነው። የኮሌጁ አሰልጣኝ ዳኛቸው ወልደሚካኤል ኮሌጁ በርካታ የቴክኖሎጂና ፈጠራ ሥራዎች እየሰራ ቢሆንም ከእነዚህ ውስጥ የተወሰኑትን በአውደርዕዩ ይዞ መቅረቡን ይገልጻሉ። ማንኛውንም አይነት የባልትና ውጤት ማቀነባበሪያ ማሽን፣ የቃጫ ማውጫ ማሽን እና የመኖ ማቀነባበሪያ ማሽኖች በአውደ ርዕዩ ቀርበዋል።

ከእነዚህ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አንዱ የሆነው በኮሌጁ አሰልጣኞች የተሰራ ማንኛውንም አይነት የባልትና ውጤት ማቀነባበሪያ ማሽን ነው። እሳቸው እንደሚሉት፤ ይህ ማሽን በተለየ መልኩ ማንኛውንም አይነት የባልትና ውጤት ለማቀነባበር ያስችላል። ማሽኑ ሦስት አይነት ሲሆን፤ አንደኛው ማሽን የባልትና ውጤቱ የሚቆላበት፣ የሚታመስበት፣ የሚደርቅበት፣ እና የሚቀዘቅዝበት ነው። ሁለተኛው ማሽን የባልትና ውጤቱ የሚፈጭበት ሲሆን ሦስተኛው ማሽን ደግሞ የሚታሸግበት ነው። እነዚህ ሦስቱ ማሽኖች የባልትና ውጤትን ከመጀመሪያ አንስቶ እስከ መጨረሻው ድረስ የሚደረገውን ሂደቶች ይከናወንበታል።

«ማሽኑ የምንጠቀማቸው የተለያዩ የባልትና ውጤቶች ሁሉንም ሂደቶች በምንፈልገው ልክ እንደራሳችን ፍላጎት እያደረግን ለመስራት የሚያስችል ነው። የተወሰኑት ጤፍ መሰል ነገሮችን አይቆላም እንጂ እንደስንዴ፣ ገብስ እና የመሳሳሉት ደግሞ የሙብሰል በሚገባው መጠን የሚያበስልና የሚቆላም ነው። እንዲሁም እንደቆሎ ለመቁላት ያስችላል» ብለዋል።

«ማሽኑ በአንድ ጊዜ እስከ 25 ኪሎ ግራም እህል የመቁላት አቅም አለው» ያሉት አሰልጣኙ፤ ይህ ማሽን ለየብቻ የተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሦስቱንም ማሽኖች በማገናኘት በአንድ ላይ ቢያያዙ ደግሞ ይበልጥ የሥራ ቅልጥፍና ይጨምራል፤ ሰዓት ይቆጥባል፤ ምርታማነትንም ይጨምራል። በማለት በቀጣይም እነዚህን ማሽኖች በአንድ ላይ በመገጣጠም እንደሚሰሩ አመላክተዋል።

ማሽኑን አብዛኛው በቀላሉ ከሚገኙ ማቴሪያሎች የተሰራ ሲሆን፤ የሚሰራው በኤሌክትሪክ ኃይል ነው። አሁን ላይ በኤሌክትሪክ ኃይል እንዲሰራ የተደረገ ቢሆንም በሌሎች ሲስተሞች እንዲሰራ አድርጎ መስራት የሚቻል መሆኑን ጠቁመዋል።

አሰልጣኙ "እንደዚህ አይነት ማሽኖች በሌላው ዓለም ላይም ያሉ ናቸው። ካሉት ውስጥ ግን ተመራጭ እና ወጪ ቆጣቢ የሆነውን እያወዳደርን የሚጨመሩት ነገሮች እየጨመርን ነው የሰራነው» ይላሉ። ከውጭ ከሚመጣው ጋር ሲነጻጸር እያንዳንዱ የማሽኑ ዋጋ የተሻለና በግማሽ ያህል ቅናሽ ያለው ነው፤ ማሽኑ በሀገር ውስጥ በስፋት የሚመረት ከሆነ ደግሞ ለበርካታ ሰዎች የሥራ እድል ይፈጥራል። ተጠቃሚውን ጥራቱን በጠበቀ መልኩ እንዲያመርት ስለሚያስችለው ምርታማ ያደርገዋል ብለዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ የሀገር ውስጥ ምርቶች ላይ የሚታየው የጥራት ችግር በሂደት የሚቀረፍ ነው። በተደጋጋሚ ሲሰራ ብዙ ነገሮች እየተስተካከሉ መሻሻሎች እየመጡ ለውጥ ማምጣት ይቻላል። ማሽኑ በአውደ ርዕዩ ከቀረበ በኋላ የሚሰጡ አስተያየቶችን በመጨመር ኢንተርፕራይዞቹ በምን መልኩ አሻሽለው መጠቀም እንደሚችሉ ምክረ ሀሳብ ይሰጣል። ማሽኑ ተባዝቶ ተሻሽሎ ለገበያ ሊውል ይችላል። አሁን ላይ የሀገር ውስጥ ምርቶች መጠቀም ላይ መሻሻሎች እየታዩ ኅብረተሰቡ የውጭውን እየተወ የሀገር ውስጥ ምርቶች እየተጠቀመ መምጣቱ አበረታች ነው።

እስካሁን የሚሰሩት ቴክኖሎጂዎች ለኢንተርፕራይዞች የሚተላለፉበት ሁኔታ እንዳለ ያነሱት አሰልጣኙ፤ ነገር ግን በቀጣይ በኮሌጁ አምርቶ እንዲያበዛ የሚደረግበት አሠራር ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን ኅብረተሰቡን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን ለማቅረብ እንደሚሰሩ ይገልጻሉ። በቀጣይ ምስራቅ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ኅብረተሰቡ ሊጠቀምባቸው የሚችለውን ቴክኖሎጂዎች በመስራት ያቀርባል ሲሉ አስገንዝበዋል።

በኮሌጁ የተሰራው ሁለተኛው ቴክኖሎጂ የቃጫ ማውጫ ማሽን ሲሆን፤ በሰልጣኞችና በአሰልጣኞች እገዛ የሰሩት መሆኑን ገልጸው፤ ይህ ማሽን ሀገር በቀል ቴክኖሎጂ ላይ የተሰራ በመሆኑ በቀላሉ ቃጫ በመፋቅ የቃጫ ውጤት የሚያቀርብ እንደሆነ ገልጸዋል።

ሦስተኛው የቴክኖሎጂ ውጤት የመኖ ማቀናበሪያ ማሽን ነው። ይህ ማሽን አነስተኛ መጠን ያለው ሲሆን በውስጥ ያለውን መፍጫ ብቻ በመቀያየር ማንኛውንም አይነት የእንስሳት መኖ ለማቀነባበር ይጠቅማል። በአሁኑ ወቅት በኤሌክትሪክ ኃይል እንዲሰራ የተደረገ ሲሆን፤ በሌሎች የኃይል አማራጮች እንዲሰራ ማድረግ እንደሚቻልም ይገልጻሉ።

ኮልፌ ኢንዱስትሪያል ኮሌጅም በአውደ ርዕዩ በርካታ ቴክኖሎጂ ውጤቶች ይዞ ከቀረቡት መካከል ይገኝበታል። አቶ ወርቅነው ሰማኝ የኮልፌ ኢንዱስትሪያል ኮሌጁ የማኑፋክቸሪንግ አሰልጣኝ ናቸው። ኮሌጁ የሸክላ መፍጫ ማሽን፣ ሻምፖና ኮንዲሽነር ማምረቻ ማሽን እና ብረት በተለያዩ ቅርጾች ለማውጣት የሚያስችል የቴክኖሎጂ ውጤቶች ሰርቷል።

የሸክላ መፍጫ ማሽኑ በአራት አሰልጣኞች የተሰራ ሲሆን፣ ይህ ማሽን ምጣድም ይሁን ማንኛውንም አይነት የተሰባበረ ሸክላ በመፍጨት ወደ አፈርነት ያቀይራል። ሸክላው ወደ አፈርነት ከተቀየረ በኋላ መልሶ ይቦካና የተፈለገውን አይነት የሸክላ ቁስ ይሰራበታል። በመሆኑም ማሽኑ በሰዓት እስከ አንድ ኩንታል ወይም መቶ ኪሎ ግራም አፈር ይፈጫል።

ማሽኑን በቀላሉ ከሚገኙ ማቴሪያሎች የተሰራ በመሆኑ ከውጭ ከሚመጣው ጋር የተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ጠቅሰው፤ ቴክኖሎጂ ከውጭ ከሚመጣ የተቀዳ ቢሆንም ከውጭ ከሚመጣው ማሽን የተሻለ እንደሆነ አመላክተዋል።

በዋጋም ከውጭ አገር ከሚመጣው ጋር ሲነጻጸር በተመጣጣኝ የሚባል ዋጋ እንዳለው ያመላክታሉ። ከውጭ የሚገባው ማሽን ለመግዛት 480 ሺ ብር የሚጠይቅ ሲሆን፤ ይህ ማሽን ግን 115 ሺ ብር እንደፈጀ ተናግረዋል። ይህ ቴክኖሎጂ ሀገር በቀል ቴክኖሎጂ በኢንተርፕራይዞች ፍላጎት መሰረት የተሰራ መሆኑን ጠቅሰዋል። «በሀገራችን ብዙ የሸክላ ሠሪዎች መኖራቸውና አብዛኛውን ጊዜ እንጀራ ለመጋገር የምንጠቀመው የሸክላ ምጣድ ስለሆነ ይህንን የሸክላ ምጣድ ለመስራት ደግሞ ሸክላ ሰሪ ባለሙያዎች የሚጠቀሙት አፈር እስካሁን ድረስ በእጃቸው የእየፈጩ ነው። በመሆኑም ማሽኑ ይህ ችግር ለመቅረፍ ታስቦ የተሰራ ነው» ይላሉ።

በመሆኑ ኅብረተሰቡ አውቆ እንዲጠቀምበት በአውደርዕይ መቅረቡን ጠቁመው፤ ማሽኑን አምርተው ለተጠቃሚ ለሚያቀርቡ ኢንተርፕራይዞች የተሸጋገረ ነው። ከዚህ በኋላ ኢንተርፕራይዞቹ ዲዛይኑን ወስደው ማምረት ይችላሉ ሲሉ አስታውቀዋል።

በተጨማሪም ሻምፖና ኮንዲሽነር ማምረቻ ማሽን ይዘው መቅረባቸውን የገለጹት አሰልጣኙ፤ ይህ ማሽን እንደሌሎቹ ማሽኖች ሁሉ በሀገር ውስጥ የተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በጥራት ሆነ በዋጋ ከውጭ ከሚመጣው በጣም የተሻለ እንደሆነ ይገልጻሉ። «በአገር ውስጥ የሚሰሩት ማሽኖች ጥራታቸው የጠበቁ ከመሆናቸው በላይ በአገር ውስጥ ሊጠገኑ የሚችሉ ናቸው» ይላሉ። ብዙ ጊዜ ከውጭ የሚመጡ ማሽኖች ለጥገናም ቢሆን የማይቻልበት እና ግዴታ ባለሙያ የሚፈልጉ ስለሚሆኑ ይህ ማሽን ግን ሁሉ ነገር ገልጸው ስለሆነ ማንኛውም መካኒክ ሊጠግነው የሚችለውን መሆኑን ገልጸው፤ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግል ተደርጎ የተሰራ መሆኑም ለየት እንደሚያደርገው አመላክተዋል።

ሌላው የሰውን ጉልበት በመቀነስ ድፍን ብረቶች ለተለያዩ ጌጣጌጦች በሚሆን መልኩ ለመስራት የሚያስችል ማሽን መስራታቸውን አንስተዋል። ማሽኑ ትልልቅ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ካልሆነ አብዛኛው ሀገር ውስጥ የሌለ መሆኑን ገልጸው፤ በሀገር ውስጥ የተሰራ በመሆኑ የሀምሳ ሺ ብር ያህል ቅናሽ እንዳለው አመላክተዋል። በተለይ ጥገና ላይ የሰራው አካል በቦታው ተገኝቶ ጥገና ማድረግ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን ጠቁመዋል።

አሁን ላይ ያሉት ሁሉም ማሽኖች የተሸጋገሩ ስለሆኑ በቀጣይ ኮሌጁ ከኢንተርፕራይዝ ፍላጎት በመነሳት ኅብረተሰቡን ሊጠቅሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን የሚሰራ መሆኑን አስታውቀዋል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ ትንታኔ

## የንብረት ማስመለስ አዋጅ - ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ

**ስምስም መንግሥቱ**

8 ክፍሎች፣ 57 አንቀጾችና ዝርዝር ሕጎች ያሉት የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጅ ለተጨማሪ ምክክርና ውይይት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቅረቡና ለቋሚ ኮሚቴ መመራቱ ይታወሳል።

ከፍትህ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ የረቂቅ አዋጁ ዋና ዓላማ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ወይንም ትርፍ ለማግኘት ተብሎ የሚፈፀም ወንጀልን ለመከላከልና ወንጀል አትራፊ መሆን የለበትም የሚል መርህ እውን ለማድረግ ሲሆን ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ ሀብት ማስመለስን የተመለከተ ነው፡፡

በዚህ በኩል ተበታትነው የተቀመጡና ወጥነት የጎደላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ወጥና ሙሉዕ የሆነ የሕግ ማእቀፍ እንዲኖር ማስቻል ነው።

በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ሁሉን አቀፍ የሆነ የተሟላ ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ፣ አራተኛው ዓለም አቀፍ ግዴታዎችን የተመለከተ እና ዓለም አቀፍ ግዴታዎችን ለመወጣትና ዓለም አቀፍ መሥፈርቶችንም ለማሟላት የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ለማድረግ ነው።

ረቂቅ አዋጁን ለማዘጋጀት ከአንድ ዓመት ጊዜ በላይ የወሰደና የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ወይንም ተሞክሮ መሠረት ያደረገ ስለመሆኑና የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮና አግባብነት ያላቸው ሰነዶች መዳሰሱን፣ በጥናቱም ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን በማሳተፍ በተቻለ መጠን ቀደም ሲል የነበሩ የሕግ ክፍተቶችን ለመመለስ በሚያስችል መልኩ ረቂቅ አዋጁ መዘጋጀቱን መረጃው አመልክቷል።

የረቂቅ አዋጁን አስፈላጊነትና ዋና ዓላማ እንዲሁም ይዘቱንና ረቂቅ ሕጉ ያለበትን ደረጃ በተመለከተ የፍትህ ሚኒስትር ጌዲዮን ጢሞቲዮስ (ዶክተር) ማብራሪያ ሰጥተዋል።

በማብራሪያቸውም እንዳስረዱት፤ ረቂቅ አዋጁ ካካተታቸው አራት መሠረታዊ ዓላማዎች አንዱና ቀዳሚው ኢኮኖሚያዊ ወንጀሎች እየተበራከቱ መምጣታቸውን አመላካች የሆኑ ነገሮች መኖራቸው ነው። ሰዎች የኢኮኖሚያዊ ጥቅም ወይንም ሀብት ለማግኘት ብለው የሚፈጽሟቸው ወንጀሎች እየተበራከቱና ውስብስብ የመሆናቸው ጉዳይም እየጨመረ መምጣቱ ነው፡፡

ሰዎች ከሕገወጥ ድርጊታቸው እንዲቆጠቡና ጥቅም እንዳያገኙ ማድረግ በአጠቃላይ እንዲህ ያሉ ወንጀሎችን ለመከላከል አዋጁን ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በወንጀል ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማግኘት የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ጉዳያቸው ወይንም ነገራቸው በእስራት ብቻ የሚያልቅ ሳይሆን፣ በወንጀል ተግባር ያፈሩት ሀብትም የሚነጠቅ፣ የሚወሰድ፣ የሚወረስ ከሆነ ወደ ወንጀል ተግባር የመሰማራት እድላቸውም ሊቀንስ የሚችል ስለሆነ እንዲህ ያሉ የረቀቁና በተደራጀ ሁኔታ የሚፈጸሙ ኢኮኖሚያዊ ወንጀሎችን መከላከል አንዱ የረቂቅ አዋጁ ዓላማ ነው። ወንጀል አትራፊ መሆን የለበትም የሚለውን መርህ እውን ለማድረግ ጭምር የታሰበበት ነው፡፡

ሀብት ማስመለስ ላይ ከዚህ ቀደም የሕግ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ተበታትነው የተቀመጡ በመሆናቸው አፈፃፀም ላይ ክፍተት ማምጣታቸውን ነው ሚኒስትሩ የጠቀሱት። እንደርሳቸው ገለጻ የሚመለስ ሀብት እንዴት ይለያል፣ ይመረመራል፣ ይጠናል፣ ይታገዳል፣ እንዴትስ ይያዛል፣ ንብረቱ በሚታገድበት ወቅት እንዴት ይተዳደራል የሚለውን የተመለከቱ ድንጋጌዎች አሁን ባሉ በተወሰኑ አዋጆች ላይ ተበታትነው ይገኛሉ። ለአብነትም ሙስና፣ ሽብርን፣ በሰዎች መነገድን ለመከላከል የሚሉት አዋጆች ይጠቀሳሉ። በነዚህ መሠል አዋጆች ተበታትነው የሚገኙ ድንጋጌዎች አሉ፡፡

የተበታተኑ አዋጆች መኖራቸው ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ሆነው ከመገኘታቸው በተጨማሪ ከአንዱ አዋጅ ወደሌላኛው አዋጅ በሚኬድበት ወቅት አፈፃፀማቸው ወጥ አይደለም። በአንደኛው አዋጅ የተከሰሰ ሰው ንብረት የሚመለስበት ሂደትና በሌላኛው አዋጅ የተከሰሰ ሰው ንብረት የሚመለስበት አካሄድ ወጥነት የሚጎለው መሆኑ እንደ አንድ ክፍተት ታይቷል፡፡

ይሄ ደግሞ በአንዳንድ ወንጀሎች የሚገኝ ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ወይንም ሀብት ማስመለስ የሚያስችል ሥርዓት እንዳይኖረን ያደርጋል። ሙሉዕ ወጥ የሆነ የሕግ ማእቀፍ እንዳይኖርም አድርጓል። ማንኛውንም በወንጀል የተገኘ



**አቶ ዓምደገብርኤል አድማሱ**



**ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በረኸተስፋ**

ሀብትን የሚመለከት ሙሉዕ የሆነ የሕግ ማእቀፍ ያስፈልጋል የሚለው ሌላው የረቂቅ አዋጁ መነሻ ነው፡፡

ሶስተኛው የረቂቅ አዋጁ መነሻ፤ ሁሉን አቀፍ የሆነ የተሟላ ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን የተመለከተው የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ ነው። ሆኖም ይህ ሕግ ሙሉ ለሙሉ አዲስ ሆኖ የመጣ እንዳልሆነ መረዳት ይገባል። አንዳንዴ ሰፋ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ጠበብ እያለ በተለያዩ አዋጆች ተካትቶ ሲፈፀም ነበር። ሆኖም የአፈፃፀም አድማሱ ላይ የተወሰነ ልዩነት እንዳለው መረዳት ይገባል ብለዋል።

እዚህ ላይ የሚስተዋለው ክፍተት ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን የተመለከተው አሁን በሥራ ላይ ያለው ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው የሕዝባዊ ድርጅቶች ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ እንዲሁም የመንግሥት ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ ነው። ይሄ መሆኑ ያስከተለው ክፍተት አንድ ሰው አሁን ባለው የሕግ ድንጋጌ ምንጩና ምክንያቱ ያልታወቀ ሀብት ቢኖርህ ሕጉ በወንጀል ተጠያቂ ነህ ቢለውም ተጠርጣሪው በተለያየ ሕገወጥ መንገድ ያገኘውን ሀብት በሌላ ሰው ስም በማድረግ ከተጠያቂነት ወይንም ከሕጉ ተፈፃሚነት ማምለጥ ይችላል። የመንግሥት ሠራተኛ ወይንም ኃላፊ ሀብትህን አስመዝግብ ሲባል ካለው ሀብት ጥቂቱን ብቻ ነው የሚያስመዘግበው።

ይህ ነው የሚባል ሥራ የሌለው ግን ደግሞ በሚሊዮን ብር የሚያንቀሳቅስ ሀብት የፈጠረ ሰው በማኅበረሰብ ውስጥም ጥያቄ እያስነሳ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ አጠራጣሪ የሆኑ ነገሮች ሲያጋጥሙ የሚጠየቅበት የሕግ ማእቀፍ የለም። ይሄ በሕግ ሥርዓት ውስጥ ትልቅ ክፍተት በመሆኑ ሙስናንም ሆነ ሌሎች ወንጀሎችን ለመከላከል፣ በአጠቃላይ ሕጋዊነትን ለማሳደግ ክፍተቱንም ለመድፈን ሌላው የረቂቅ ሕጉ መነሻና ዓላማ ነው ሲሉም አብራርተዋል፡፡

አራተኛው ዓላማ ዓለም አቀፍ ግዴታዎቻችን ለመወጣትና ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ እንደሆነ የጠቀሱት ሚኒስትሩ፤ ሀብት ማስመለስን በተመለከተ ሀገራት ምን አይነት የሕግ ማዕቀፍ ሊኖራቸው ይገባል የሚለውን የተመለከተ ድንጋጌ ያላቸው የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መኖራቸውን ነው የገለጹት። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሙስናን ለመከላከል በብዙ ሀገራት የፀደቀ ዓለም አቀፍ ስምምነት መኖሩን አመልክተዋል፡፡

የተደራጁ ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ ወንጀሎችን የተመለከተ የተባበሩት መንግሥታት ዓለም አቀፍ ስምምነት መኖሩንና እኤአ ከ2000 በኋላ ባለፉት 20 እና 30 ዓመታት ይሄን ጉዳይ የተመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ሰነዶች እየወጡ ስለመሆናቸው አስረድተዋል። ዓለም አቀፍ አደረጃጀቶችና ሌሎችም መሰል የሚጠቀሱ አደረጃጀቶች መኖራቸውን ጠቅሰዋል።

በዓለም አቀፍ ስምምነትና አደረጃጀቶች በሚያወጧቸው ምክረሀሳቦች ሀገራት ንብረት ማስመለስን የተመለከተ ሕግ ሊኖራቸው እንደሚገባ፣ ሕጎቹ ደግሞ ሊኖራቸው ስለሚገባው ይዘት የተቀመጡ መስፈርቶችና ግዴታዎች መኖራቸውን፣ ግዴታዎችና መስፈርቶቹም ሰነዶች ላይ ብቻ ተቀምጠው የሚቀሩ እንዳልሆኑ፣ ሀገራትም ግዴታዎቻቸውን በአግባቡ ስለመውጣታቸው ይገመገማል ሲሉም አስረድተዋል።

እንዲህ ያለ ሕግ በሌለ ቁጥርና አሁን ያሉት የሕግ ክፍተቶች ላይም ማሻሻያ ካልተደረገ እና እርምጃ ካልተወሰደ የኢኮኖሚ ወንጀሎች እየተበራከቱና እየተራቀቁ ይሄዳሉ ያሉት ሚኒስትሩ፤ ወንጀሎቹ በገነገኑ ቁጥር አጠቃላይ ፖለቲካል ኢኮኖሚው የነጣቂ፣ የዘራፊና የቀማኛ የማድረግ እድሉ ሰፊ እንደሚሆን አመልክተዋል።

ሕግ አክብረው ለሚሰሩ የማይመች፣ ሕግ ለማያከብሩ ደግሞ እንደልባቸው ሀብት የሚያፈሩበት ኢኮኖሚ እንዳይሆን እንዲህ ያለ አዋጅ አስፈላጊ እንደሆነ ታምኖበታል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

የረቂቅ አዋጁን አስፈላጊነት ያመኑበት አካላት ቢኖሩም በተቃራኒው የተወሰኑ ወገኖችን ለመጉዳት ታስቦ የተዘጋጀ አዋጅ እንደሆነ በማንሳት የሚከራከሩ አልጠፉም። በዚህ መልኩ ረቂቅ አዋጁ አነጋጋሪ ሆኖ ሰንብቷል።

አዋጁን መሠረት አድርጎ እየተነሱ ባሉ ጉዳዮችና ኢኮኖሚውን ለመጠበቅ አዋጁ ያለውን ፋይዳ ሀሳባቸውን እንዲሰጡን የጋበዝናቸው በኢፌዴሪ የሕገመንግሥት አጣሪ ጉባኤ ከፍተኛ የሕገመንግሥት ተመራማሪ አቶ ዓምደገብርኤል አድማሱ እንደሚከተለው አብራርተዋል።

እንደ አቶ ዓምደገብርኤል፤ አዋጁ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊም የተለያዩ ሀሳቦችን እያስተናገደ በባለሙያዎችም የተለያዩ ትችቶች እየቀረቡ እንደሆነ መከታተላቸውን ገልጸዋል። እርሳቸው እንዳሉት አዋጁ ገና በውይይት የሚዳብር በመሆኑ ያለቀለት ሕግ ተደርጎ መውሰድ የለበትም። በረቂቅ አዋጁ በስፋት በትችት የተነሱትም በውይይት የሚዳብሩበት እድል ይኖራል የሚል እምነት አላቸው።

የተወሰኑ አካላትን ለመጉዳት የወጣ አዋጅ ነው ብለውም አያምኑም። አንድ ወቅት ላይ የፀረሙስና አዋጅ ሲወጣ ለምን ታስቦ እንደወጣ ይታወቅ እንደነበር ከሚያስታውሱት ውጭ የሆነ አካል ለመጉዳት የወጣ አዋጅ በታሪክ እንደሌለ ነው የገለጹት።

ንብረት የማስመለስ ረቂቅ አዋጅ በጥቅሉ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከማስጠበቅ አንጻር ፋይዳው የጎላ ሆኖ እንዳገኙት የሚናገሩት አቶ ዓምደገብርኤል፤ በተለያየ መንገድ የሕዝብ ሀብትና ንብረት ተዘርፎ የተለያዩ ሰዎች ከብረውና በልጽገው የታየበት ጊዜ ያለፉት 30 እና 40 ዓመታት ተሞክሮን እንደማሳያ አንስተዋል። የሕዝብ ሀብት ዘርፈው የከበሩ ሰዎች ሀብቱን በምን መልኩ እንዳገኙ ወይንም እንዳካበቱ ተጠያቂ ሲሆኑም ሆነ፣ በሕገወጥ ያፈራችሁት ሀብት ነው ተብለውም ሲወሰድባቸው ወይንም ሲወረስ አለመታየቱን ነው ያስረዱት።

እንደ ሀገር ጉዳት እያስከተሉ ካሉ ወንጀሎች በሕገወጥ መንገድ የሚፈጠር ሀብት እንደሆነ ያነሱት አቶ ዓምደገብርኤል፤ ጉዳቱም የሀገር ኢኮኖሚ እድገት እንዲጎዳ፣ እንዲዳትት ብልሹ አሰራርም እንዲስፋፋ፣ ሕገወጦች እንዲከብሩ፣ በማድረግ ይገለጻል ብለዋል።

አሁን ላይ የተዘጋጀው ንብረት የማስመለስ ረቂቅ አዋጅ ኢኮኖሚውን ይታደገዋል የሚል እምነት አላቸው። አዋጁ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማፋጠን፣ መልካም አስተዳደርን በማስፈን፣ ዜጎች ሀብትን በሕጋዊ መንገድ ለማፍራት እንዲነሳሱ፣ በአንድ ጀንበር ሚሊየነርና የሕንፃ ባለቤት የሚኮንበት ታአምራቶች እንዲቆሙ በማድረግ ሚናው ከፍተኛ እንደሚሆን ገልጸዋል።

አቶ ዓምደገብርኤል፤ እንደስጋት ያነሱት የሕግ ተፈፃሚነቱ ላይ ነው። የሕግ የበላይነት መላላት ሳይሆን፣ የሕግ መፈጸም ችግር መኖሩንና እስካሁን ባለው ሁኔታም ሕግ እንዲፈጸም ምቹ እንዳልነበር አውስተዋል። ይሄም በጠንካራ ተቋም ያለመመራት ክፍተት እንደሆነ ይገልጻሉ። ንብረት የማስመለስ ረቂቅ አዋጅ ፀድቆ ሥራ ላይ ሲውል ሕጉ በአግባቡ ከተፈጸመ እንደሀገር ጥቅሙ የበዛ ሊሆን እንደሚችል ነው የተናገሩት፡፡

የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በረኸተስፋ የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጅ አስፈላጊ መሆኑንና አሰራሩ በሌሎች ሀገሮችም መኖሩን ነው የገለጹት። በኢትዮጵያ ሙስና መንሰራፋቱን አመላካች የሆኑ ነገሮች መኖራቸውንና ቀድሞ መሰራት የነበረበት እንደነበር አመልክተዋል።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ‹‹አንድ ሰው አላግባብ በሆነ መንገድ ሀብት ሲያፈራ መንግሥት በተለያየ መንገድ መቆጣጠር አለበት›› ብለዋል። አሁንም ሀገሪቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት አጋጥሟት፣ የኢኮኖሚ ጭንቀት በተፈጠረበት ወቅት በአንዳንድ ሱቆች ውስጥ የሚያዙት የእቃ አይነቶችና የመሸጫ ዋጋቸው ጥያቄ የሚፈጥሩ መሆናቸውንና ከጀርባ ያለው ነገር እየተፈተሸ እንዳልሆነ አንስተዋል።

ምሁሩ አክለውም ከዘረፋ ጋር በተያያዘ በተለይም የመንግሥት ለውጥ ከተደረገ በኋላ ብዙ ነገሮች መሰማታቸውን ገልጸዋል። አሁንም ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል የሚሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ ሰዎችን እያስፈራሩ ገንዘብ የሚቀበሉ ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ስጋታቸውን ገልፀዋል፡፡

ረቂቅ አዋጁ ብዥታንም እየፈጠረ መሆኑንና በዚህ በኩልም ግንዛቤ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል። ከውጭ በሚመጣ ገንዘብ ላይ በተለያየ መንገድ የሚሰራጨው መረጃ በዋናነት ዲያስፖራውን እንዳስደነገጠው ጠቁመዋል። እንደ ምጣኔ ሀብት ባለሙያው ገለጻ፤ እንዲህ አይነት ሕጎች ሲወጡ የሙያ ማኅበራት የተሳተፉበት ሕዝባዊ ውይይቶች ያስፈልጋሉ።

ከሙስናና ምዝበራ ጋር በተያያዘ አፍሪካ ሀገሮች ስማቸው በመልካም ነገር አይነሳም ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ የመንግሥት ኃላፊዎች ስልጣናቸውን ተጠቅመው ብዙ ነገር እንደሚያደርጉ በየጊዜው የሚነገር እንደሆነም ጠቁመዋል።

በሙስና ወንጀል ስማቸው ከፍ ብሎ ከሚነሱ ሀገራት ናይጄሪያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ኬኒያ ለአብነት ጠቅሰዋል። ኢትዮጵያ ሙስናን ለመከላከል ጥሩ ተሞክሮ ያላቸውን ሀገሮች ልምድ ለመቅሰም የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሲንጋፖር መሄዳቸውን አስታውሰዋል።

ዓለም ውስጥ ሙስናን እየተዋጉ ያሉት ኢንቨስትጌቲቭ ሚዲያ (የምርመራ ጋዜጠኝነት) እና የሲቪክ ማኅበራት ናቸው። እንደ እድርና መሰል ማኅበራት በማኅበረሰብ ውስጥ ምን እየተፈፀመ እንደሆነ ያውቃሉ ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ ኢትዮጵያ ውስጥም የሲቪክ ማህበራት ተደራጅተው ሙስናን ለመከላከል መስራት እንዳለባቸው፣ የምርመራ ጋዜጠኝነትም መጠናከር እንዳለበትና በነዚህ አካላት ትብብር ኢኮኖሚውን መታደግ እንደሚቻል ገልጸዋል። መንግሥትም ለነዚህ ተቋማት ከለላ በመስጠት ማበረታታት እንዳለበት አመልክተዋል፡፡

ሙስና የሕዝብን የእለት ተእለት ኑሮ የሚጎዳ እንደሆነ ግንዛቤ ተይዞ ካልተሰራ መንግሥትም በዚህ ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ ካልወሰደ ሕዝብ በምርጫ እንዳያሸንፍ ሊያደርገው እንደሚችልም ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ገልጸዋል፡፡

በንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጅ ላይ እንዲህ ሀሳባቸውን የሰጡት ባለሙያዎች በሕጉ ተፈጻሚነት ላይ ትኩረት እንደሚያስፈልግ አስምረውበታል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# በሯጭነት እና በወታደርነት ለሀገር የተከፈለ ውለታ

**አስመረት ብስራት**

መቼም የሰው ልጅ ፍላጎቱን እንጂ የሕይወት መንገድ የት እንደሚያደርሰው አይታወቅም። ሕይወት ራሷ መርታ ያልታሰበና ያልታለመ ቦታ ላይ ስታኖረን አሜን ብሎ ከመቀበል በቀር ምን ይባላል። የሕይወት መስመር ከራስ ፍላጎት ወጥቶ በእድል መመራቱን ማሳያ የሆነችን ሴት ታሪክ ለዛሬ የሴቶች አምድ ይዘንላችሁ ቀርበናል። የዛሬ ባለታሪካችን እንደ አብዛኞቹ የአርሲ አካባቢ ልጆች የሩጫ ፍላጎትም ክህሎትም የነበራት ነበርች። በትምህርት ቤት ውድድር አያያዟን የተመለከቱ መምህራን ኢትዮጵያን በዓለም አደባባይ ከሚያስጠሩት አትሌቶቻችን አንዷ ልትሆን እንደምትችል ይናገሩ ነበር። ነገር ግን የሕይወት መስመር ተቀይሮ ባላሰበችው መንገድ ውስጥ እንደቆመች የምትናገረውን ሴት ታሪክ በዚህ መልኩ አቅርበነዋል።

ኮማንደር በሻዱ ደበሌ ከእናቷ ወይዘሮ ሙሉ መልካ ከአባቷ አቶ ደበሌ አሸኖ በ1961 ዓ.ም ነበር የተወለደችው። ኮማንደሯም የተወለደቸው አርሲ ዞን ሊሙና ቡሉቡሌ ወረዳ ኡሉሌ ሀሳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ነው። በሻዱ ከተወለድችባት ቀዬ ትምህርት ቤት ለመድረስ ከአንድ ሰዓት ተኩል በላይ የሚወስደውን መንገድ እየሮጠች ትደርስ ነበር። በዘጠኝ ዓመቷ የአስኳላን ደጅ የረገጠችው ይቺ ልጅ ትምህርት በጣም የምትወድ ስለነበረች ወላጇቿ ከትምህርት ቤት እንዳያስቀሯት በማለት በጥዋት ተነስታ ውሃ ቀድታ ቤት ውስጥ የሚጠበቅባትን ስራ ሰርታ በሩጫ ወደ ትምህርት ቤት ትሄድ እንደነበር ታስታውሳለች።

ከትምህርት ቤትም በሩጫ ተመልሳ እናቷን የምትረዳ በመሆኗ አያያዟን ያዩ መምህራኖቿ በትምህርት ቤት ደረጃ እየተወዳደረች ውጤት እንድታስመዘግብ ያበረታቷት ነበር። ከትምህርት ቤት የተጀመረው ውድድር ወደ ወረዳ ከፍ ሲል፣ ከዛም ወደ አውራጃ ሲያድግ አርሲ ክፍለ ሀገር በሚባል በመወዳደር ከዛ ወደ ማረሚያ ቤት ክለብ ተቀላቀለች።

ማረሚያ ስፖርት ክለብ ውስጥ ለሁለት ዓመት በስልጠናና በውድደር ካሳለፈች በኋላ ወደ ውትድርና ማሰልጠኛ ገባች። በወቅቱ መቶ ሜትር ሁለት መቶና አራት በመቶ ሪሌ ሁልጊዜም አንደኛና ሁለተኛ ትወጣ ነበር።

በወቅቱ አጠራር ከአርሲ ክፍለ ሀገር ከሊሙና ቡልቡሌ ወረዳ ከመራሮ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መጥተው ከትምህርት ቤት ወደ ቤት ከፋጡማ ሮባ ጋር አድርገው በመውሰድ ቤተሰቦቻቸውን አስፈቅደው፣ ከአሰላ ከተጨመሩ ወደ ስምንት ከሚጠጉ ልጆች ጋር በ 1979 ዓ.ም ነበር ማረሚያ ቤት የስፖርት ክለብን የተቀላቀለችው። የማረሚያ ቤት ስፖርት ክለብን እንድትቀላቀል ያደረጓት ሀጂ ቡልቡላና መቶ አለቃ ተገኝ አለማየሁ የተበሉ ሰዎች እንደነበሩ ትናገራለች።

ይህች ታዳጊ ወጣት በሻዱ ደበሌ አሸኑ ስትባል ከተወለደችባት ቀዬ ውስጥ ሯጭ መሆን ከሚችሉ ወጣቶች መካከል አንዷ መሆኗ ተነግሯት ነበር ከቤቷ የወጣችው። ሯጭ የመሆን ሕልሟን በልቧ ሰንቃ እንደሷ ተመርጠው ከመጡ ወጣቶች ጋር በመሆን ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ስፖርት ክለብ ውስጥ ማረፊያቸው ሆነ። ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ስፖርት ክለብ ካምፕ ውስጥ እየኖሩ ልምምድ እያደረጉና የተለያዩ ውድድሮችን እየተወዳደሩ እያለ ነበር ሯጭ ለመሆን ተፈጠረኩ የምትለው ወጣት በ1980 ዓ.ም ወደ ሚሊተሪ ክፍል እንድትዘዋወር የተደረገው።

ወደ ውትድርና ክፍል የመዘዋወሪዋ ምክንያት ያልተገለጠላት ይህች ሴት “ እኔ ከእናት ከአባቴ ተለይቼ የወጣሁት ሯጭ ለመሆን እንጂ ወታደር ለመሆን አይደለም»። በማለት ለምን ወደዚያ ክፍል ተዛወርኩ ? “ ብላ በምትጠይቅበት ጊዜ፤ የመስሪያ ቤቱ ሕግ መሆኑንና ከስፖርቱ እኩል ውትድርና መሰልጠን የግድ መሆኑ ይነገራታል።

በወቅቱ አሁን ታዋቂ ሯጭ የሆነቸው ጌጤ ዋሚና ሌሎች አትሌቶች አንድ ላይ ሆነው ወደ ወታደር ማሰልጠኛ ከገቡ በኋላ እዛው ባሉበት ኮማንደሯ ቀድማ የምትወዳደርበትን አጭር ርቀት ትታ ወደ ስምንት መቶና አራት መቶ ሜትር የሩጫ ዘርፍ (ፊልድ) በመቀየር የተሻለ ውጤት ለማምጣት ትጥር ጀመር። በወቅቱ አትሌት ጌጤ ዋሚ የነበረችበት ሁኔታ (ኮንዲሽን) በጣም ጥሩ ስለነበር የማሰልጠኛውን ስልጠና አቋርጣ በውድድር እንድትሳተፍ ተደረገ። በተሳተፈችበት ውደድርም ውጤታማ ሆነች።

ሌሎች ማሰልጠኛ የገቡ አትሌቶች ግን ስልጠናቸውን አጠናቀው ሲወጡ ወደ ስፖርት ክለቡ እንቀላቀላለን ብለው ቢጠብቁም የሆነው ግን ወደ ስፖርታዊ ወድድርና ወደ ወታደራዊ አገልግሎት የሚሄዱትን በእጣ የመለየት ሁኔታ ነበር። ወጣቷ በሻዱም እጣዋ በውትድርና እንድታገለግል የሚል ሆነና ፍቼ ማሪሚያ ቤት ደርሷት እዛ ስድስት ወራት አገለገለች። የውትድርና ሕይወትን በግድም ቢሆን ተቀብላ በስራዋ ውጤታማ ለመሆን የምትጥረው ኮማንደር በፍቼ ማሪሚያ ቤት ስድስት ወራትን ካገለገለች በኋላ በዝውውር መርሃ ቤቴ አውራጃ ዓለም ከተማ ተልካ አንድ ዓመት አገለገለች።

በወቅቱ የደርግ መገርሰስና ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ሊመጣ ያለበት የሽግግር ጊዜ ላይ ነበር ዓለም ከተማ ውስጥ የውትድርና ስራ ላይ ተሰማርታ የነበረው። ያኔ ወያኔ ጠንክሮ ዓለም ከተማን ሲቆጣጠር በወቅቱ የነበሩት ወታደሮች ስራቸውን ትተው ወደ ትውልድ ቀያቸው ለመመለስ ተንቀሳቀሱ። ሁሉም ወታደር ተነስቶ ጉዞ ሲጀምር ገና በአፍላው የወጣትነት እድሜዋ ሊያውም ሳትፈልግ የተቀላቀለችውን የውትድርና ሕይወት ጥላ ለመሄድ እሷም ተነሳች።

የተመደበችበትን ስራ ትታ ወደ እናትና አባቷ ቤት ለመሄድ የተነሳችው ኮማንደር እደርሳለው ብላ ካሰበችበት ሳትደርስ መሀል ሜዳ የተባለ ቦታ ለቀናት መታሰራቸውን ታስታውሳለች። ወታደር በመሆናቸው የተነሳ ጥቃት ሊያደርስባቸው ላለ ሁሉ አፀፋ መልስ እየሰጡ ጉዞ ላይ የነበሩት ወታደሮች በሰፊው ተጠቅተው ጉዳት ደረሰባቸው። እሷም እግሯን ተመታች። ቤተሰቧ ጋር ለመሄድ የወጣችው ወታደርም በመቁሰሏ የተነሳ ደብረ ብርሃን ሆስፒታል ገብታ ቆየች።

ቀደም ሲል አባቷ ከስፖርተኞች ክለብ ወጥታ ውትድርና ማሰልጠኛ መግባቷን ሲሰሙ ከሷ ቀድሞ ልጆቻቸውን ለውትደርና ሰጥተው አለመመለሳቸውን አንሰተው “ ይህች ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች ብርቅዬ ልጄን ድጋሚ ለጦርነት አልማግድም “ በማለት አሌልቱ ማሰልጠኛ ድረስ በመሄድ ልጄን ስጡኝ ብለው እንደነበር ታስታውሳለች።

ያኔ የመከላከያ ክለብ ስፖርተኞች በሙሉ የውትድርና ስልጠና እንደሚወስዱ ተነግሯቸው ተረጋግተው ቤታቸው ተመልሰው እንደነበር ታስረዳለች። ደርግ ተገርስሶ ኢህአዴግ ሲገባ መራቤቴ የነበሩ ወታደሮች ሞቱ፤ ተማረኩ ቆሰሉ መባሉን የሰሙት አባት በፊት ሳያምኑበት ልጃቸው ወታደር መሆኗም ሲያሳዝናቸው ስለኖሩ፤ በድንጋጤ ግፊታቸው ጨምሮ ሕይወታቸውን ሊያጡ ቻሉ። ከሞት የተረፈች አንድ ልጃቸውን መልሼ ልውሰድ እያሉ ተከልክለው ለሞት አሳልፈው መስጠታቸው ከአእምሮ በላይ ሆኖባቸው ሞቱ።

ኮማንደርም በአባቷ ሞት ምክንያትና፤ ከቁስሏ እስክታገግም ድረስ ወደ ትውልድ ቀዬዋ ተመለሰች። ኮማንደር ሀዘኑ ከሆዷም ባይወጣ፤ ለሀገር ግዳጅ ተጠርታለችና ከቁስሏም እንዳገገመች ወደ ማረሚያ ቤት ተመለሰች። በደብረ ብርሃን ማረሚያ ቤት ተመድባ እንድትሰራ ቢነገራትም የማረሚያ ቤቱ ኃላፊዎች ጋር ቀርባ በወቅቱ የነበረባት ተደራራቢ ችግር በማስረዳቷ የተነሳ ከደብረ ብርሃን ወደ አሰላ ማረሚያ ቤት ተዛውራ እንድትሰራ ተወሰነላት። ከዛ በኋላ የተመደበችበትን ግዳጅ እየተወጣች ጎን ጎን ልትሆን ለምትፈልገው አትሌትነት የሚያግዛትን ልምምድ ታደርግ ጀመር።

ያለፍላጎቷ ወታደር የሆነችው ኮማንደር ሕልሟን እውን ለማድረግ ሌት ተቀን ብትለፋም፤ አሸንፋ ለመታየት ብትጥርም ሳይሳካላት ቀረ። የእድሜ መጨመር፤ ጉዳትና ሌሎች ምክንያቶች ተጨማምረው ሯጭ ለመሆን ከቤቷ የወጣችውን ወጣት እድል በመራት መንገድ እንድትጓዝ አስገደዳት።

በፍላጎቷ ያለመችበት ያልደረሰችው ኮማንደር የተሰጣትን በመውደድ ኃላፊነቷን በአግባቡ መወጣት ጀመረች። ሕልሟ እውን ሊሆን እንደማይችል ስትረዳ በተሰማራችበት ሀገሯን ለማገልገል የተሻለ ስራ ለመስራት መጣር ጀመረች። ከልብ የሆነው ጥረትም ፍሬ አፍርቶ ኃላፊነት ቦታ ላይ እየተመደበች ስታገለግል መቆየቷን ትናገራለች።

በሰለጠነችበት የውትድርና ሙያ የተለያዩ የውትደርና ደረጃዎች ላይ በመመደብ የተለያዩ ክልሎችንና ወረዳዎችን እየተዘዋወረች ማገልገል ጀመረች። በዚሁ በውትድርና ሙያዋ ጡረታ እስክትወጣ ድረስ ስታገለግል ቆየች።

ኮማንደር በሻዱ እንደምትለው “በወቅቱ ታዋቂ ስፖርተኛ ከነበሩት ከአትሌት ጌጤ ዋሚ፤ ከአትሌት ፋጡማ ሮባና ከአትሌት ደራረቱ ቱሉ ጋር የተወዳደርኩ፤ ውጤት ማምጣት እየቻልኩ በግድ ወታደር የሆንኩ በመሆኔ ከልብ አዝናለሁ” ትላለች።

አሁን ጡረተኛ የሁለት ወንድ ልጆች እናት ናት፤ ትምህርቷን አቋርጣ ራጭ የሆነችው ልጅ ስራ ላይ ሆና ትምህርቷን በመከታተል ውጤታማ ሆናለች። አሁን ሰው ሃብት አስተዳደር በዲፕሎማ ተመርቃለች።

እድል ምን ጊዜም የራሷ የሆነ መንገድ አላት። አንዳንዶች በለፉት ልክ የእድል መንገዳቸውን አግኝተው ስኬታማ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ምን ቢጥሩ ሕልማቸውን መኖር ላይችሉ ይችላሉ። ይህ የሚጠበቅና የትም ያለ ሃቅ መሆኑን መረዳት ግን እጅግ አስፈላጊ ነው።



ኮማንደር በሻዱ ደበሌ

**እኔ ከእናት ከአባቴ ተለይቼ የወጣሁት ሯጭ ለመሆን እንጂ ወታደር ለመሆን አይደለም»። በማለት ለምን ወደዚያ ክፍል ተዛወርኩ ? “ ብላ በምትጠይቅበት ጊዜ፤ የመስሪያ ቤቱ ሕግ መሆኑንና ከስፖርቱ እኩል ውትድርና መሰልጠን የግድ መሆኑ ይነገራታል**

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

**ከትላንቱ ለዛሬ፤ በአዲስ ዘመን ድሮ ከወጡ ልዩ ልዩ ጉዳዮች መካከል ጥቂቶቹን በመምረጥ አቅርበንላችኋል። በሀገራችን ውስጥ የጥንታዊ ታሪክ ከመገኘቱ ጋር በተያያዘ በወቅቱ የነበረው ጭምጭምታ፣ ተቆጣጣሪ በመምሰል የሚያጭበረብረው ሰው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጉዳዩ የጤና ባለሙያዎችን እያከራከረ የነበረን አንድ ጉዳይ ልናስታውስ ነው። እንዲሁ ደግሞ —አዲሱ ትውልድ ለምን ቶሎ ይገረጅፋል?" ምርምር ባዘለው ጥያቄ ከአዲስ ዘመን ሌላኛውን ገጽ እናስታውስበታለን።**

### የጥንታዊ ታሪክ ቦታ መገኘት ጭምጭምታ

በአሩሲ ጠ/ግዛት፣ በጭላሎ አውራጃ፣ በጢዮ ወረዳ በዱግዳ ም/ጠቅላይ ግዛት ባላምባራስ ዓምደ ቡታ ባላባትነት ልዩ ስሙ ቲሮ ኞሮ በተባለው ጭው ያለ በረሃ አገር ይገኛል።

.............

በዚሁ ቀበሌ ገለቶ ጦሪ የተባለው ሰው በበረሃው ውስጥ ሲዘዋወር አንድ ከፍተኛ ቦታ ላይ ይበቅላል ተብሎ በማይታሰብበት የደጋ እንጨት ጥድና የመሳሰለውም ጫካ ሆኖ በቅሎ አገኘው። በዚሁ ነገር ተደንቆ ወደ ጥዱ ጫካ እገባለሁ ሲል በማይታሰብበት ቦታ የጠራ ውሀና በዚያው አጠገብ ፍልውሃ አገኘ። ከውሃውም አጠገብ አጽፍ(ቆዳ) የለበሰ ፀጉሩ እንደ ባሕታዊ በትከሻው ላይ የወረደ ለአራዊት ውሃ መጠጫ ቦታ ሲያዘጋጅ በደረስሁበት ጊዜ በቁጣ ቃል "ምን ልታደርግ መጣህ? ከመጣህበት ተመልሰህ ሒድ፤ ያየኸውንም ሁሉ እንዳትናገር የተናገርህ እንደሆነ እስከ ሕይወትህ ያሠጋሃል" ብሎ ተናገረ።

ከዚህም በቀር ሌሊቱን በሕልሜ በመዓልት (ቀን) እንደ ገሠጸኝ አደርሁ። በዚሁ ሳልወሰን ተግሣጹን ሳላከብር በማግሥቱ ቦታው እንዳይጠፋብኝ እንጨት እየሰበርሁ በመንገድ እየጣልሁ ተመልሼ ነበርና ያንን ምልክት በመከተል በዚያ ቦታ ስደርስ ከየት መጣ ሳልል ድምፁን በመስማት ብቻ በጥፊ ቢመታኝ አንድ ዓይኔ ታወረ። አንድ ዓይኑ እስካሁንም እንደታወረ ነው።

ዳግመኛ እንደዚሁ ቦባሳ በዳሳ የሚባለው ይህንኑ የጥንታዊ ታሪክ ቦታ በማግኘት በዚያ ቦታ በመገኘቱ ብርቱ ተግሣጽ አግኝቶት እንዳይናገርም መከልከሉንና ሊናገር ጥቂት ጊዜ ቀርቶታል ተብሎ መነገሩን ገልጿል።

ብዙዎች ሰዎች እንዲያሳዩኝ ስጠይቃቸው የበቃ መነኩሴ አብሮ ካልሔደ አይሆንም በማለት ለመሔድ አይፈቅዱም። ይህንንም ሁኔታ ያገኘሁት ከባላምባራስ ዓምደ ቡታ ልጅ ከአቶ ገና ዓምደ ነው። በዚሁ በተባለው ቦታ አካባቢ ኃይለኛ እንደ አውሎ ነፋስ የሚተፋ ዋሻ የሚገኝበት መሆኑን በማስረዳት ነግሮኛል።

ከዚህም ጋር በአጠገቡ የድንጋይ ከሰል በብዛት መገኘቱንና በመሐንዲስ ለመመርመር የሚያስፈልግ መሆኑን ገልጿል።

(አዲስ ዘመን፣ ሰኔ 16 ቀን 1944 ዓ.ም)

### ተቆጣጣሪ በመምሰል ያጭበረበረው ተቀጣ

ደሴ፤ ኢዜአ፡- በደሴ ከተማ ውስጥ ምንም አይነት ሥልጣን ሳይኖረው የአሥር አለቃ ነኝ በማለት ከገጠር ወደ ከተማ የሚገባውንና የሚወጣውን እህል፣ ስኳርና ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጦች በመፈተሽ ሲያወናብድ የተገኘው ዓሊ መሐመድ በ3 ወር እስራት እንዲቀጣ የ04-01-01 ቀበሌ ማኅበር የፍርድ ሸንጎ ከትናንት በስቲያ ወስኖበታል።

በተከሳሹ ላይ የእስራት ቅጣት ሊወሰንበት የቻለው ባልተሰጠው ሥልጣን በመንገድ ላይ እየጠበቀ ስኳርና ሸቀጥ ጭነው ወደ ገጠር የሚወጡትንና እህል ጭነው ወደ ከተማ የሚገቡትን መኪናዎች እያስቆመ በመፈተሽ የተመቸውን ጥቅም በመቀበል ሲለቅ ያልተመቸውን ደግሞ ወደ 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ በማቅረብ አወናብዶ ለማስቀጣት ሞክሮ እንደነበር በማረጋገጡ ነው፡፡

አዲስ ዘመን፣ የካቲት 19 ቀን 1969 ዓ.ም)

### ጉዳዩ የጤና ባለሙያዎችን እያከራከረ ነው

ጫት አነቃቂ ከሆኑት ከሻይ፣ ከቡናና ከአልኮል እንጂ ከአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ጋራ አይመደብም ሲሉ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ምሑር አስታወቁ። አንድ የጤና ጥበቃ ኤክስፐርት ደግሞ ጫት ከአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች እንደሚመደብ ገለጹ።

ዶ/ር መኮንን ሐጎስ፣ በመመኮ የተባለው የግል ድርጅት አማካሪ ሰሞኑን ለጋዜጣዊ ሪፖርተር በሰጡት መግለጫ ጫትን ጨምሮ በአንድ ሺ አምስት መቶ ዕፅዋት ላይ ጥናት ሲያደርጉ መቆየታቸውንና በጥናታቸውም ጫት ከአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ሊመደብ እንደማይቻል ማረጋገጣቸውን ተናግረዋል።

ማንኛውም ነገር ከመጠን በላይ ከተወሰደ ጎጂነት እንዳለው የገለጹት ዶ/ር መኮንን በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች መቆጣጠሪያ፣ መከላከያ ቡድን ከፍተኛ ኤክስፐርት የሆኑት አቶ አብርሃም ገብረ ጊዮርጊስ ጫትን ከካናቢስና ኮኬይን ጋር ይመደባል በማለት ለመገናኛ ብዙኃን በቅርቡ የሰጡት መግለጫ የተሳሳተ ነው ብለዋል። ጫትን ከአደንዛዥ ዕፆች መመደብም ፍጹም ኢ-ሳይንሳዊ መሆኑንም አስምረውበታል፡፡

(አዲስ ዘመን፣ ታኅሣሥ 29 ቀን 1990 ዓ/ም)

### አዲሱ ትውልድ ለምን ቶሎ ይገረጅፋል

"ለተሟላ ጤንነት ለእድሜ ብልፅግና የተመጣጠነ ምግብ ተመገቡ" ይለን ነበር እስከቅርብ ጊዜ ሳይንስ አሁን ግን ነገሩ የተገላቢጦሽ ሊሆን ምንም አልቀረውም። ከወላጆቹ ይልቅ እንደ ነገሩም ቢሆን የሚመገበውን ምግብ የተመጣጠነ ለማድረግ የሚጥረው አዲሱ ትውልድ "ፋፋ ጀነሬሽን" ለእርጅና ሲጣደፍ ልብ ሳይሉ አልቀሩም። አባት በ30ኛው የእድሜ ዘመኑ የወለደው ልጁ ገርጅፎ የአባቱ የረዥም ጊዜ ጓደኛ መስሎ ሲታይ የትላንትዋ ማሚቱም ገርጅፋ አምስት የወለዱ እናትዋን ልትመስል መከጀልዋን ሲታዘቡ "ዋ እቴ የዛሬ ዘመን ልጆች ቶሎ ይወድቃሉ (ያረጃሉ)" ሲባል መሠማቱ የተዘወተረ ሆኗል፡፡

.................................

ለረዥም ጊዜ በእንስሳት ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት "አይጦችም ሆኑ ሌሎች እንስሳት ዝቅተኛ የኃይል መጠን ያላቸውን ምግቦች ሲመገቡ ረዥም ዕድሜ ይኖራሉ። ጤነኛ ይሆናሉ"

(አዲስ ዘመን፣ ኅዳር 20 ቀን 1992 ዓ.ም)

# ዓለም አቀፍ




## ሰሜን ኮሪያ የቴሌቪዥን ስርጭቷን ወደ ሩሲያ ሳተላይት ቀየረች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሰሜን ኮሪያ የቴሌቪዥን ስርጭቷን ወደ ሩሲያ ሳተላይት ቀየረች

ሰሜን ኮሪያ የመንግሥት ቴሌቪዥን ስርጭቶች የሚተላለፉበትን ከቻይና ወደ ሩሲያ ሳተላይት መቀየሯን የደቡብ ኮሪያ ዩኒፊኬሽን ሚኒስቴር ገልጿል።

ይህ ክትትል ለሚያደርጉ የደቡብ ኮሪያ የመንግሥት ኤጀንሲዎች እና ሚዲያዎች አስቸጋሪ ያደርገዋል ተብሏል።

የሰሜን ኮሪያ ሴንትራል ቴሌቪዥን ስርጭት ቀደም ሲል ይተላለፍ የነበረበትን ቻይናሳት12 ሳተላይት በመተው በሩሲያው ኤክፐረስ103 ሲተላለፍ መታየቱን ሮይተርስ የደቡብ ኮሪያውን የዲሽ አገልግሎት ጠቅሶ ዘግቧል።

የሳተላይት ቅየራው የተካሄደው፣ የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በፒዮንግያንግ ጉብኝት ካደረጉ እና ከመሪው ኪም ጆንግ ኡን ጋር ወታራዊ ስምምነት ከተፈራረሙ በኋላ ነው።

የሰሜን ኮሪያን ቴሌቪዥን አሁንም በኦንላይን ማየት ቢቻልም፣ ጥራቱ አነስተኛ ነው።

የሚተላለፉት ይዘቶች በእቅድ የተዘጋጁ እና ፖለቲካዊ ቢሆኑም ዝግ ከሆነችው ሀገር የሚገኘው መረጃ ውስን ስለሆነ የደቡብ ኮሪያ መንግሥት እና ሚዲያዎች የሰሜን ኮሪያን ሚዲያዎች ይከታተላሉ።

ሰሜን ኮሪያ የቴሌቪዥን ስርጭቷን ወደ ሩሲያ ሳተላይት ካዛወረች በኋላ የሳተላይት ስርጭቱ በተወሰኑ የደቡብ ኮሪያ ቦታዎች እንደማይሠራ የገለጸው የዩኒፊኬሽን ሚኒስቴሩ የቴክኒክ ችግሩን ለመፍታት እየሠራ መሆኑን አክሎ ገልጿል።


በደቡብ ኮሪያ የተፈቀደላቸው አካላት የሰሜን ኮሪያን ሚዲያዎች ይመለከታሉ፤ የደቡብ ኮሪያ ሕዝብ ግን እንዲያይ አይፈቀድለትም።

ሩሲያ በአሜሪካ የሚመራውን የምዕራባውያን ጥምረት ለመገዳደር ከሰሜን ኮሪያ ጋር ያላትን ግንኙነት ወደ አዲስ ምዕራፍ ስታሳድግ፣ ቻይና ከሌሎች ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ሊያወሳስብ የሚችል ስምምነት ከማድረግ ታቅባለች።

ፑቲን እና ኪም በቅርብ በፒዮንግያንግ በፈረሙት የሁለትዮሽ ስምምነት መሠረት፣ ጥቃት በሚሰነዘርባቸው ወቅት አንዳቸው ለሌላኛቸው ሁሉንም አይነት ወታደራዊ ድጋፍ ይሰጣል።

## ከእስር ቤት ሸጉጥ ነጥቀው ያመለጡት የፓኪስታን እስረኞች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ፓኪስታን ከምታስተዳድረው የካሽሚር ግዛት 18 እስረኞች ማምለጣቸው ተነገረ፡፡

እስረኞቹ የማረሚያ ቤት ጠባቂ ሽጉጥ በመቀማት አስፈራርተው ከእስር ቤት ማመለጣቸው ነው የተሰማው። ራዋላኮት ከተሰኘው እስር ቤት ካመለጡት እስረኞች መካከል ስድስቱ የሞት ፍርደኞች ሲሆኑ ሦስቱ ደግሞ የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት የተፈረደባቸው እንደሆኑ ታውቋል፡፡

የአካባቢው ፖሊስ አዛዥ ሪያዝ ሙግሀል ከእስረኞቹ መካከል አንደኛው ከፖሊስ በተተኮሰበት ጥይት ሕይወቱ ማለፉን የተናገሩ ሲሆን ቀሪዎቹን በቁጥጥር ስር ለማዋል ከፍተኛ አሰሳ እየተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

መሰል የእስረኞች ማምለጥ በፓኪስታን ያልተለመደ በመሆኑ ጉዳዩ አጋጣሚ ወይስ ታስቦበት የተደረገ ነው በሚል ምርመራ እየተከናወነ መሆኑ ተሰምቷል፡፡

እስረኞቹ በወቅቱ በጥበቃ ላይ የነበረ የማረሚያ ቤት ፖሊስ እጅ ላይ ሽጉጥ በመንጠቅ ከእስር ቤት ማምለጣቸው ሲነገር ሁኔታው አጋጣሚ ስለ መሆኑ ከፍተኛ ጥርጣሬን አጭሯል፡፡

በአሁኑ ወቅት የእስር ቤቱን ዋና ኃላፊ ጨምሮ በቀኑ ተረኛ የነበሩ ጠባቂዎች ከሥራ የታገዱ ሲሆን ምርመራው በነዚህ አካላት ላይ ያተኩራል ነው የተባለው፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ 11 ነጥብ 5 ሚሊዮን እስረኞች ሲኖሩ አሜሪካ በቁጥር ቀዳሚዋ ናት በሀገሪቱ 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን የሚጠጉ እስረኞች የሚገኙባት ሲሆን ቻይና በ1 ነጥብ 7 ሚሊዮን እስረኞች ትከተላለች፡፡

ብራዚል፣ ሕንድ፣ ቱርክ፣ ሩሲያ እና ሜክሲኮ በርካታ እስረኞች ከሚገኙባቸው ሀገራት መካከል ይጠቀሳሉ። በየዓመቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሺዎች የሚቆጠሩ እስረኞች ከተለያዩ እስር ቤቶች ያመልጣሉ፡፡

ጠንካራ የእስር ቤት ጥበቃ እና ሥርዓት እንዳላት የሚነገርላት አሜሪካ በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ እስረኞች ከሚያመልጡባቸው ሀገራት መካከል በአንደኛ ደረጃ ትገኛለች። እ.አ.አ. በ2019 ከአሜሪካ የተለያዩ እስር ቤቶች 2231 እስረኞች ማምለጥ ችለው ነበር፡፡

ጤናማ የእስረኞች ምጣኔ ከመቶ ሺህ ሰዎች መካከል 140 ሰዎች ብቻ ሊሆኑ እንደሚገባ የሚነገረው የመንግሥታቱ ድርጅት፤

ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል አለመኖር እንዲሁም ሰዎች ሕግን በራሳቸው እጅ ለማስከበር የሚወስዱት እርምጃ መጨመር ወንጀሎች እንዲበራከቱ እና የእስረኞች ቁጥርም በዛው ልክ እንዲያሻቅብ ምክንያት መሆኑን ድርጅቱ በስጋት መልክ ያነሳዋል፡፡

# ስፖርት





# የቀድሞ የአፍሪካ እግር ኳስ ከዋክብት በሸነን አፍሪካ ፌስቲቫል

ብርሃን ፈይሳ

በዓለም ላይ እያደጉ ካሉ ሃገራትም በእጅጉ ተጠቃሚ እየሆኑ ካሉባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ የስፖርት ቱሪዝም ነው። በጅማሬ ላይ የምትገኘው ኢትዮጵያም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት አበረታች ስራዎችን በማከናወን ላይ ትገኛለች። ከዚሁ ጋር ከሚጠቀሱ ክንውኖች መካከልም ከሰሞኑ በተለያዩ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦችን ያሳተፈው ሸነን አፍሪካ ፌስቲቫል አንዱ ነው። ለሶስት ቀናት የተካሄደው ይኸው አህጉር አቀፉ የፋሽን፣ የቱሪዝም እና ስፖርት ፌስቲቫልም የስፖርት ቱሪዝምን ከማነቃቃት አኳያ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

በፌስቲቫሉ ከተከናወኑ መርሃ ግብሮች መካከል አንዱ ስፖርታዊ ክንውን ሲሆን፤ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የተሳተፉበት የወዳጅነት ጨዋታ ከቀድሞ የእግር ኳስ ከዋክብቱ ጋር በወዳጅነት ፓርክ ቁጥር ሁለት ተደርጓል። አንጋፋዎቹ የናይጄሪያ ብሄራዊ ቡድን ተጫዋቾች ኑዋንኮ ካኑ፣ ዳንኤል አሞካቺ፣ ታሪቦ ዌስት እንዲሁም በአውሮፓ ሊጎች የተጫወተው ሴኔጋላዊው ሄንሪ ካማራ ደግሞ በፌስቲቫሉ ላይ የተገኙ ስፖርተኞች ናቸው።

የእግር ኳስ ጨዋታውን ተከትሎም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫን ለማስተናገድ ጥያቄ ማቅረቧን አመላክተዋል። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ዋንጫ መስራች ሃገራት መካከል አንዷ ናት። ይሁንና በመድረኩ ያላት የተሳትፎም ሆነ የአዘጋጅነት ታሪክ በሂደት እየደበዘዘ በመምጣቱ የእግር ኳስ ቤተሰቡ በትዝታ እንዲገደብ ሆኗል።

የአህጉሪቱን ትልቁን የእግር ኳስ ውድድር በማስተናገድ የስፖርት ቤተሰቡን ምኞት ዕውን ለማድረግ መንግስት ጥያቄ አቅርቦ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን በማከናወን ላይ እንደሚገኝ ተጠቁሟል።

የአፍሪካ ዋንጫን ማስተናገድ ውስብስብ ሂደቶችን እንደሚጠይቅ የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከወቅቱ የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ጋርም በጉዳዩ ላይ ውይይት መደረጉን ጠቁመዋል። የአፍሪካ ዋንጫ በኢትዮጵያ መካሄዱ የኢትዮጵያን እግር ኳስ ከማነቃቃት ባሻገር ለገጽታ ግንባታ እና ቱሪዝም ዘርፍ መነቃቃት ትልቅ ፋይዳ አለው። ከዚህ አኳያ የአፍሪካ ታላላቅ የቀድሞ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው ይህንን የኢትዮጵያ ውጥን ለማስተዋወቅ ትልቅ እድል ይፈጥራል። ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የኢትዮጵያን ገጽታ በማሳየት የነበረውን ጉልህ ሚና በመጥቀስም በቀጣይ የፈረስ ጉግስን ጨምሮ በተለያዩ ስፖርት ዘርፎች የሚሰሩ ስራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉም አረጋግጠዋል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

የቀድሞዎቹ የአፍሪካ እግር ኳስ ከዋክብቱ ከእግር ኳስ ጨዋታው ባለፈ በችግኝ ተከላ አረንጓዴ አሻራቸውን ያሳረፉ ሲሆን፤ የተለያዩ የልማት ስራዎችንም ጎብኝተዋል። ይህንን ተከትሎም አርሰናልን ጨምሮ በአያክስ፣ ኢንተርሚላን፣ ዌስትብሮሚች እና ፖርትስማውዝ ክለቦች የተጫወተው ኑዋንኮ ካኑ፤ ኢትዮጵያ እጅግ ውብና የሚያስደንቅ ባህል ያላት ሀገር መሆኗን ገልፀዋል። በኢትዮጵያ በነበራቸው ቆይታ የነበረው አቀባበልና እንክብካቤ ቤታቸው ያሉ ያህል እንዲሰማቸው በማድረጉ በቀጣይም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ እንደሚመጣ፤ እንዲሁም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለኢትዮጵያ ያላቸውን ራዕይ መሰረት አድርገው እያከናወኗቸው ያሉ የልማት ስራዎችን ስለመጎብኘታቸውም ተናግሯል፡፡

ሌላኛው ናይጄሪያዊና የቀድሞ የኢንተር ሚላን እና ኤሲ ሚላን ተጫዋቾች ታሪቦ ዌስት በበኩሉ፤ በኢትዮጵያ እየተከናወኑ ያሉ የልማት ስራዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሀገር ባለፈ ለአፍሪካ ያላቸውን ራዕይ እንደሚያሳዩ መገንዘቡን አመላክቷል። የጠቅላይ ሚኒስትሩን የአፍሪካ ዋንጫ ኢትዮጵያ እንድታስተናግድ በማድረግ የሀገሪቱን እግር ኳስ የማነቃቃት እቅድ እውን እንደሚሆን ያለውን መልካም ምኞት ገልጿል። የቀድሞ የአህጉሪቱ ታላላቅ ተጫዋቾች ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው ከኢትዮጵያውያን ጋር ትስስር በመፍጠር የእግር ኳስ ባህል እንዲሻሻል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። የናይጄሪያ ብሄራዊ ቡድን አባል የነበረው ሌላኛው ተጫዋች ዳንኤል አሞካቺ በቆይታቸው ኢትዮጵያውያን በክብርና በፍቅር አቀባበል እንዳደረጉላቸው ተናግሯል።



የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የተሳተፉበት የወዳጅነት ጨዋታ ከቀድሞ እውቅ እግር ኳስ ተጫዋቾች ጋር

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ ወ/ሪት ትዕግስት ይበልጣል እና በተከሳሾች እነ አቶ ያለም ጥላሁን አቶ ያለም ጥላሁን መካከል ስላለው የፍ/ብሄር ክርክር ጉዳይ 1ኛ ተከሳሽ መከሰስዎትን አውቀው 4/11/2016 .ም በ4፡00 ሰዓት የተቀጠረ መሆኑን አውቀው ፌ/ከ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 12ኛ ልዩ ልዩ ፍ/ብሃር 6ፎቅ ቀጥታ ክስ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል። የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

አመልካች አክሊሉ ጤራ ጭሻ እና ተጠሪ አቦነህ ንጉሴ ኤዬ መካከል ባለው የመጥፋት ውሳኔ ጉዳይ ፍ/ቤቱ ባዘዘው ትዕዛዝ መሰረት ተጠሪ ለቀጠሮው 28/10/2016 ዓ.ም እንዲቀርብ ሲል የአ/አበባ ከተማ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት አ/ከ/ክ/ም/ችሎት አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ ችሎት**

የፍ/ባለመብት/በከሳሽ ወ/ሮ ፀጋ ገብረጊዮርጊስ እና የፍ/ባለእዳ በተከሳሽ አቶ ጫሊ እጀታ መካከል ስላለው አፈፃፀም ክስ ጉዳይ ተከሳሽ በ2/11/2016 ዓ.ም ስለሆነው ቀጠሮ ከቀኑ 8፡00 ሰዓት የ/መ/ደ/ፍ/ቤት ለሚኩራ ምድብ 1ኛ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የለሚ ኩራ ም/ችሎት**

አመልካች ወ/ሮ ህብስቴ አበባየሁ ወንድም እና ተጠሪ አቶ ያየህ መኮንን ገላው ተጠሪ ሰኔ 5 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የጠፉ ስለሆነ የመጥፋት ውሳኔ ይሰጥልኝ ሲሉ አመልክተዋል። ስለሆነም ተጠሪ ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ ሀምሌ 2 ቀን 2016 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ አ/አ/ከተማ የ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቃቂ ቃሊቲ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቃቂ ም/ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች አቶ ከተማ ቡሎ ገሚሉ በተከሳሽ/ተጠሪ ዘውድነሽ ወልዱ ሽፈራ መካከል ስላለው የፍ/ብሄር ክርክር ጉዳዩ ተከሳሽ በጋዜጣ በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ እንዲደረግላቸው ፍ/ቤቱ ያዘዘ በመሆኑ ለሐምሌ 02/2016 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መናገሻ ምድብ 3ኛ ችሎት ያዘዘ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ ንብ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ እና በተከሳሽ ካሳሁን ግርማይ ተኮላ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 5ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በፅሁፍ በ01/11/2016 ዓ.ም በ8፡00 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት በ03/11/2016 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ይዘው እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ችሎት**

በአመልካች ወ/ሮ ትርሃስ ገ/ጊዮርጊስ ንጉሴ እና በተጠሪ አቶ ገ/የሱስ ግደይ ገ/መድህን መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሣሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ ለ5/11/2016 ዓ.ም 3፡30 ሰዓት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በይግባኝ ባይ እነ አቶ ገመቹ ለማ በመልስ ሰጪ አቶ ጻጋዬ ተ/ማርያም መካከል ባለው የፍትሃብሔር ክርክር ጉዳይ ለመልስ ሰጪ አቶ ጻጋዬ ተ/ማርያም ለሐምሌ 08 ቀን 2016 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ጠዋት 03፡30 ሰዓት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት 1ኛ ፍትሃብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

በይግባኝ ባይ ብርሃን ባንክ አ.ማ በመልስ ሰጪ እነ አቶ ዘካሪያስ ታደሰ /2ሰዎች/ መካከል ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ 1ኛ መልስ ሰጪ አቶ ዘካሪያስ ታደሰ ለ ሀምሌ 05 ቀን 2016 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጧዋቱ 4፡00 ሰዓት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት 2ኛ ፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

በአመልካች ብርሃን ባንክ አ.ማ በተጠሪ እነ ሃብታሙ እንግዳው (3ሰዎች) መካከል ባለው አፈጻጸም ክርክር ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ሃብታሙ እንግዳው እና 2ኛ ተጠሪ አምደሚካኤል ተመስገን ለ ሃምሌ 01 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡10 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት ሬጅስትራር ቢሮ እንዲቀርቡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት 2ኛ ሰበር ሰሚ ችሎት አዟል፡፡

**ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ አቶ ሰለሞን ፀጋዬ እና በተከሳሽ ኤ.ኤፍ.ኢ.ኤ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሣሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 1ኛ ፍ/ብሐር አየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሑፍ ለ4/11/2016 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

ይግባኝ ባይ አቶ ዘላለም ታምራት ከበደ መ/ሰጪ እነ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና መ/ቤት 2ኛ አቶ አሊ አብዱራህማን መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ 2ኛ መልስ ሰጪ ይግባኝ መጠየቁን አውቀው ለ28/10/2016 9፡00 ሰዓት የተቀጠረ መሆኑን አውቀው ፌ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ተስፋ ኮኮብ ት/ቤት አካባቢ 7ኛ ይግባኝ ፍትሃብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል። የማይቀርቡ ቢሆን ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**